# የእግዚአብሔር ፍቅር፤ የእኛ ህይወት

## ክፍል ሁለት

በጃኪ.ይ ኦሼክ

### የክርስቶስ ስቃይ፤ ሞት እና ትንሳኤ ታሪኮች
### ከማቴዎስ ፤ ከማርቆስ፤ ከሉቃስ እና የዮሐንስ መፅህፍት
### የተወሰዱ ታሪኮች

ትምህርት 1: እነሆ! ልጆሽ — ኢየሱስ፤የእኔ ምሳሌ
ትምህርት 2: አምላኬ፤አምላኬ — ተተወ
ትምህርት 3: ሂድና ተናገር! — እርሱ ተነስቷል!
ትምህርት 4: አይኖቻቸው ተከፈቱ — የትንሳኤ ቀን
ትምህርት 5: እኔ እልካችኋለሁ — ኢየሱስ፤ የእኔ ሰላም
ትምህርት 6: ትወደኛለህ? — በጎቼን መግብ
ትምህርት 7: ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ — የኢየሱስ ትዕዛዝ

"አንተን እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።"

መዝሙር 119:11

በቴንዝፓምር ፐብሊሽንግ የተዘጋጀ

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው ©2015 በክሮስኮኔክት ሚኒስትሪ

ይህንን ጥናት ያለ አዘጋጁ የፅሁፍ ፈቃድ ማንኛውንም ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ማባዛት ሆነ ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል።

በጥናቱ ውስጥ የጠቀሱት ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1962 ዓ.ም. እትም የመፅሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው።

# ትምህርት አንድ

# እነሆ! ልጅሽ

## ሉቃስ 23 እና ዮሐንስ 19 — ኢየሱስ፤ የእኔ ምሳሌ

---

**የትምህርት አንድ ምልከታ**


ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 1: ሉቃስ 23፤ ዮሐንስ 19

- ከመስቀል የተነገሩ የመጀመሪያዎቹ ቃላት
- 1 ጴጥሮስ 2:20-23 — ኢየሱስ፤ የእኛ ምሳሌ
- ኢየሱስ፤ የዋሁ ወንጀለኛ
- የርህራሄ ልጅ
- ርህሩህ ሁኑ

## መግቢያ

ኢየሱስ ተሰቅሏል። የእርሱ ሰውነት በህመም ተጎሳቁሏል። ለመተንፈስ እየታገለ ነው። የእርሱ አፍ በውሃ ጥም ምክንያት ደርቋል። በደም የተለወሰው ሰውነቱ ዓለም ሁሉ እየተመለከተው በመስቀል ላይ ተንጠልጥሏል። ምን እንኳን እየተሰቃየ ቢገኝም ኢየሱስ ገና ያልፈፀመው ስራ አለው። ሊገመት በማይችል ስቃይ ውስጥ ቢሆን እርሱ የተናገራቸውን ነገሮች እስቲ እናድምጥ። “ አባት ሆይ ይቅር በላቸው!” “ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ።” “ እነሆ ልጅሽ።” ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት “እኔን ያየ አብን አይቶአል” (ዮሐንስ 14:9) በማለት ተናግሯል። እነዚህን የኢየሱስን ቃላት ስትሰሙ ስለእርሱ አባት ማንነት ወይንም ተፈጥሮ መገንዘብ ትችላላችሁ። እርሱ እንደ አባት ኢየሱስ ደግሞ እንደ ልጅ።

ከጥቂት አመታት በፊት ኢየሱስ አስራ ሁለት ሰዎችን እንዲከተሉት ከጠራቸው በኂላ የሰው አጥማጆች እንደሚያደርጋቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። በመስቀል ላይ እየተሰቃየ ባለበት ጊዜ እንኳን በምሳሌ አስተምሯቸዋል። በጴጥሮስ መልዕክቶች (1 ጴጥሮስ 2) ስለኢየሱስ ግብዣ እና የእርሱን ፈለግ በመከተል መከራን እና ስደትን እንድንቋቋም ጴጥሮስ ያበረታታናል። እንድንከተለው የጠራን ጌታ እንድናደርግ ከእኛ የሚፈልገው ነገር እርሱ ከተቀበለው መከራ አንፃር እጅግ ትንሽ ነው። ኢየሱስ በመከራው ውስጥ በፅናት እንዲቆም ያደረገው ነገር ምን እንደሆነ ተመልከቱ።

ኢየሱስ በመከራው እና በሞቱ ያደረገላችሁን ነገር ተጠቃሚ እንድትሆኑ እንጋብዛለን። እርሱ በእኛ ፈንታ ያለጥፋቱ እና በደሉ ስለተሰቃየ እና ስላዳነን ከልባችሁ አመስግኑት። ይህ እግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ “ ስለእኛ ሲል እግዚአብሔር ኃጢአት ያላወቀውን አንዲያ ልጁን ኃጢአት አደረገው፤ በዚህም እኛ የእግዚአብሔር ፅድቅ እንድንሆን ነው ።”

## ትምህርት 1

<u>ምዕራፍ 1</u>

### መግቢያ

ኢየሱስ ከጠዋቱ ሶስት ሰዓት (ሶስት ሰዓት -- ማርቆስ 15:25) ጀምሮ እስከ ቀኑ ዘጠኝ ሰዓት (ዘጠኝ ሰዓት — ማርቆስ 15:34) ድረስ በመስቀል ላይ ነበር ። የወንጌል ፀሀፊዎች እንደዘገቡት ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተንጠልጥሎ እያለ ሰባት ጊዜ ተናግሯል። ኢየሱስ የተናገራቸውን እነዚህን ነገሮች እንመለከታለን። አሁንም እንደገና የምናበረታታችሁ ወደ መስቀሉ እንድትቀርቡ ነው። ኢየሱስ ደክሟል ለሞትም ተቃርቧል። የእርሱ ቃላትን ለማዳመጥ ያስቸግሩ ይሆናል ቢሆንም ኢየሱስ የሚናገራቸውን ለማድመጥ ጥረት አድርጉ።

**የቤት ስራ**: ሉቃስ 23:34ሀ በድጋሚ አንብቡት። እንደገና ኢየሱስ ምን አለ?

____________________________________________________________

### መልመጃ:

1. ኢየሱስ እጆቹ እና እግሮቹ በሚስማር እንደተቸነከሩ የተናገረውን የመጀመሪያውን ቃላት ሉቃስ ዘግቦልናል። መስቀሉ፣ ሰውነቱ በደረሰበት ግርፋት፣ እንግልት እና በሚስማር መቸንከር የተነሳ እጅግ እየተሰቃየ የሚገኘውን ኢየሱስን ተሸክሟል። ኢየሱስ በመጀመሪያ የተናገረው ቃላት፣ “አባት ሆይ፣ ________________________________________በላቸው።”
2. ከታሪክ የምንማረው በመስቀል ላይ ተሰቅለው በሞት እንዲቀጡ የሚደረጉ ሰዎች እርቃናቸውን ሆነው ሰዎች ሁሉ ውርደታቸውን እንዲመለከቱ ይደረጋል። ወታደሮቹ የእርሱን ልብሶች እጣ ተጣጥለው እየተከፋፈሉ በመሆናቸው ኢየሱስ ምን ሊናገር እንደሚችል መገመት እንችላለን (ቁጥር 34ለ)። ኢየሱስ የቀረው ነገር የለም። እርሱ ልብሱን እንኳን ተገፍፎ እርቃኑን እያለ ለጠላቶቹ እንዲህ ብሎ ፀለየ፣ “ አባት ሆይ፣ ______________________አያውቁም እና ______________ በላቸው።” እነርሱስ ምን እያደረጉ ነው?

   ________________________________________________________

   ኢየሱስ አባቱን አንዲያ ልጁን እያሰቃዩ ያሉትን ሰዎች ይቅር እንዲላቸው ጠየቀ።

### ማሰላሰል

ይህንን ጥናት ስናሰላስል አንድ ቀላል ጥያቄን እስኪ ራሳችንን እንጠይቅ፣ “እኔ ምን አደረግሁ?” ነገር ግን መጠየቅ ያለብን ይህንን ጥያቄ ነው? ማድረግ የሚገባ ነገር ቁጭ ብለን በጥሞና ኢየሱስ

ያደረገውን ነገር ማስላሰል ነው። ኢየሱስ ምንም ኃጢአትን አላደረገም። ኢየሱስ የእርሱን ተከታዮችን፤ ጵላጦስንም፤ ሆነ ማንንም አላታለለም። እርሱ እንደ ቃሉ የሚሆን እና የሚያደርግ ነው። ሰዎች ሁሉ ሲሰድቡት እና ሲያስፈራሩት ኢየሱስ አልተበቀለም። ነገር ግን ኢየሱስ " በፅድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ(1 ጴጥሮስ 2:22-23)።" በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## <u>ምዕራፍ 2</u>

**ትግበራ**:

1. ኢየሱስ ማድረግ የሚገባውን አደርጓል፤ እርሱ ያደረገው ነገር ለህይወቴ ምን ዓይነት ትርጉም አለው? 1 ጴጥሮስ 2:24 አንብቡት።

   ________________________________________________________________

2. ኢየሱስ በአገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ የተራራው ስብከት ተብሎ የሚታወቀውን አስተምሯል። ይህ ትምህርት በማቴዎስ ምዕራፍ 5፤ 6፤ እና 7 ላይ ሙሉ በሙሉ ይገኛል። የኢየሱስ ትምህርት ማቴዎስ 5:44 አንብቡት። "እኔ ግን እላችኋለሁ:

   ________________________________________________________________"

3. ኢየሱስ ያስተማረው ትምህርት እርሱ በሚያቋቋመው መንግስት ውስጥ መሆን ስላለበት ስርዓት ሲሆን እርሱ ራሱ ጠላቶቹን _______________ በማለት እና ለእነርሱ በመፀለይ እኛም ጠላቶቻንን ____________________ እንድንል ምሳሌ በመሆን አስተምሮናል። ኢየሱስ ሰው ሁሉ የሚመለከተው ትክክለኛው የእግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ኢየሱስ በሰዎች መካከል ልዩነት የማያደርገውን የአባቱን የእግዚአብሔርን ፍቅር በተግባር አሳይቷል ።

4. ኢየሱስ መከተል የሚገባኝን የህይወት ንድፍ ስላሳየኝ እኔም በእያንዳንዱ ቀን እግዚአብሔር የእኔን ህይወት በመጠቀም በዙሪያዬ ለሚገኙ ሰዎች የእርሱን ፍቅር ለማሳየት ፈቃደኛ ነኝ?

   ________________________________________________________________

**ማስታወስ**

ኢየሱስ ምሳሌን ትቶልናል። የእርሱ ምሳሌነት እኛ ልንከተለው የሚገባን ፍፁም የሆነ ንድፍ ነው። ጴጥሮስ በ1ጴጥሮስ 2:20ለ-21 ላይ የሚነግረን ነገር ምንድነው? "...ነገር ግን ____________አድርጋችሁ መከራን ስትቀበሉ ____________፥ ይህ ነገር ____________ ዘንድ ____________ ይገባዋል።____________ ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ

____________እንድትከተሉ ____________ትቶላችሁ ስለ እናንተ ____________ተቀብሎአልና።"

ይህን ጥቅስ በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፉትና ለህይወታችሁ ምን ማለት እንደሆነ አሰላስሉት…

- መላካም ነገር አድርጎ መከራን መቀበል
- በትዕግስት መከራን መቀበል
- ለፅድቅ ሲሉ መከራን ለመቀበል መጠራት
- የእርሱን ፍለጋ መከተል

**ፀሎት**

1 ጴጥሮስ 2:20ለ-24 ውስጥ እንደተፃፈው ኢየሱስ በተወልን ምሳሌ መሰረት የግል ፀሎታችሁን ፃፉ ።

____________________________________________________

____________________________________________________

## ምዕራፍ 3

**መግቢያ**

ኢየሱስ ለጠላቶቹ ከፀለየ በኋላ አብረውት ከተሰቀሉት እስረኞች መካከል ከአንዱ ጋር ያደረገውን ንግግር ሉቃስ ዘግቦታል ። በመጀመሪያ ሁለቱም ወንጀለኞች "ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዶች ደግሞ ያንኑ እያሉ ይነቅፉት ነበር (ማቴዎስ 27:44)።" አሁን ግን በሉቃስ 23:40 ላይ አንዱ ወንጀለኛ ሌላው ወንጀለኛ ሲገስፀው እንመለከታለን።

**የቤት ስራ**: ሉቃስ 23:41-43 አንብቡት።

**ማሰላሰል**

አንዱ ወንጀለኛ ለሌላው፤ "ስለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው" ብሎ ገሠጸው። ይህ ሰው ጥፋቱን ተናዘዘ። ማድረግ የማይገባውን ነገር እንዳደረገ አመነ። ለዚህ ደግሞ ተመጣጣኝ ቅጣቱ ሞት ነው። ይቅርታ እንደሚያስፈልገው ተገነዘበ። ኢየሱስን፤ "….አስበኝ " ይቅር በለኝ አለው።

**ትግበራ**

እኔስ እንዴት ነኝ? የትኛውን ወንጀለኛ እመስላለሁ፤ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ኢየሱስን የሚያላግጥበትን ወይንስ የራሱን ጥፋት ተገንዝቦ አዳኙ ኢየሱስ እንዲያስበው ምህረት የጠየቀውን?

____________________________________________________

**ማሰላሰል**

አንዱ ወንጀለኛ ሌላውን፤ "ይህ ግን ምንም ክፉት አላደረገም" ብሎ ገሠጸው:: እንደገና ኢየሱስ ምንም ጥፋት እንዳላጠፋ ተረጋገጠ። ቀደም ብሎ ጵላጦስ በኢየሱስ ላይ ምንም ጥፋት እንዳለገኘበት ተናግሮ ነበር። እርሱ ንፁህ ሰው ነው!

**ትግበራ**

1. እኔ የኢየሱስን ንፁህ ሰው መሆን ለመቀበል እና ለሌሎች ሰዎች ለመስከር ፈቃደኛ ነኝ? በእኔ ህይወት ውስጥ ለሆኑ መጥፎ ነገሮች ሁሉ ተጠያቂ የማደርገው ኢየሱስን ነው?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

2. ስለእርሱ የማምነውን ነገር የእኔ ህይወት እንዴት ነው የሚያፀባርቀው?

   ______________________________________________________________

**ማሰላሰል**

1. ከዚያ በኋላ ጥፋቱን የተናዘዘው ወንጀለኛ የሚያስገርም ነገር እንዲህ ብሎ ተናገረ፤ "ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ ::" ይህ ሰው ኢየሱስ ንጉስ እንደሆነ አይኖቹ ተከፍተው ተመለከተ። እርሱ እነዚያ ሰዎች ኢየሱስን እየቀለዱበት የአይሁድ ንጉስ፤ እስራኤል ንጉስ እያሉ ሲሰድቡት ሰማ። ከኢየሱስ ራስ ላይ ተፅፎ የተለጠፈው ፅሁፍ: "የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ" የሚል ነበረ (ዮሐንስ 19:19)። ምንም እንኳን ሰዎች ሁሉ ኢየሱስን እየሰደቡ ቢቀልዱበትም ይህ ሰው ግን ኢየሱስ ንጉስ እንደሆነ አወጀ።
2. ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ፤ የእስራኤል ንጉስ፤ የአይሁድ ንጉስ ብሎ ያወጀውን ይህንን ወንጀለኛ ይቅር አለው። ለኢየሱስ ይህ ሰው ለእርሱ አባት ለእግዚአብሔር አብ ክብርን የሰጠ፤ በልጁ አማካኝነት ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ እና እውነትን እንዲያውቁ የሚወድደውን እግዚአብሔር አብን የአወቀ ሰው ነው (1 ጢሞቴዎስ 2:4)።

**ትግበራ**

በእርግጥ ኢየሱስ የእስራኤል ንጉስ ነው። ኢየሱስ የእኔም ንጉስ መሆን ይፈልጋል። ልክ እንደዚህ ሰው እኔም ኢየሱስ ንፁህ ሰው መሆኑን እውቅና እሰጣለሁ? እኔን እንዲያስበኝ እና ይቅር እንዲለኝ እጠይቀዋለሁ? የእርሱ ንጉስነት በማወጅ ኢየሱስን የህይወቴ ጌታ ነው ብዬ እቀበላለሁ? ከሁሉ በላይ ኢየሱስ ፤ "እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" ብሎ የሚናገረኝን እሰማለሁ?

______________________________________________________________

______________________________________________________________

**ፀሎት**

"እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ" ብሎ ኢየሱስ ለወንጀለኛው የተናገረውን ቃላት በማሰላሰል ፀልዩ።

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**የቤት ስራ**፤ ዮሐንስ 19:25-27 አንብቡት። ስለእነዚህ ቃላት በወንጌሉ ውስጥ የሚነግረን ዮሐንስ ብቻ ነው። እነዚህ ቃላት የተነገሩት ለኢየሱስ ቅርብ ለሆኑ ሰዎች ነው፤ የእርሱ እናት እና "ኢየሱስም ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ (ዮሐንስ 13:23)፤" እርሱም ዮሐንስ።

**ጥያቄ**

ኢየሱስ ለእናቱ ምንድነው ያለው?

____________________________________________________________

ኢየሱስ ለዮሐንስስ ምን አለው?

____________________________________________________________

**መልመጃ**:

1. በመስቀሉ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሰዎች እነማን ናቸው (ቁጥር 25)?

   ________________________________________________________________

2. ኢየሱስ ማንን ነው የተመለከተው (ቁጥር 26)?

   __________________________________________________

3. በአጠገቡ የቆመው ማነው (ቁጥር 26ለ)

   ______________________________________________

4. ኢየሱስ እናትን ለልጅ እና ልጅን ለእናት አስረከበ። ቁጥር 27ለ የሚናገረን ምንድነው?

   ________________________________________________________________

**<u>ምዕራፍ 4</u>**

**ማሰላሰል**:

1. ኢየሱስ ሊሞት ተቃርቧል። ዘግናኙን ህመም እየተቋቋመ ነው። በመሞት ላይ ያለውን ልጇን ፀጥ ብላ እንባዋን እያፈሰሰች የምትመለከተው እናቱን ተመለከተ። በአጠገቧ ደግሞ ዮሐንስ ቆሟል። ልባችን ለማርያም ያዝናል ። በደም ተለውሶ ነፍሱ እያጣጣረ ልጇን ስትመለከት ምን እንደሚሰማት አስቡ። ይህች እናት ቢሆንላት በግርፋት እና በሚስማር የቆሳሰለው ልጇን ከመስቀል አውርዳው ቁስሎቹን ብታስታምመው ደስታዋ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ በመስቀል

ላይ እንደተሰቀለ ነው፡፡ ማርያም በጥልቅ የውስጥ ህመም እየተሰቃየች ነው፡፡ እርሷና ዮሴፍ በሉቃስ 2:35 ላይ ህፃኑ ዮሴፍን ወደ ቤተ መቅደስ በአመጡ ጊዜ ስምኦን ምን ብሎ ነው የተናገራ

______________________________________________________

2. ኢየሱስ እናቱን እና ወዳጁን እንደተመለከታቸው ተነግሮናል፡፡ ኢየሱስ እነርሱን የተመለከተው በርህራሄ ዓይኖቹ ነው፡፡

ሀ. በማቴዎስ 9:36 ኢየሱስ ብዙ ____________________ባየ ጊዜ፥ ___________________ እንደ ሌላቸው ________________________ ተጨንቀው _______________________ነበርና ________________________ ::

ለ. በማቴዎስ 14:13-14 የምንመለከተው ኢየሱስ ፀጥ ወዳለ ቦታ ሄደ፤…ነገር ግን በሐይቁ ሌላኛው አቅጣጫ ሲደርስ ብዙ ህዝብ ተመለከተና የራሱን የጥሞና ጊዜን ተወ፡፡ "ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ከዚያ ______________________ ወደ ምድረ በዳ ______________________ ፈቀቅ አለ፤ ______________________ ሰምተው ከከተማዎቹ______________________ተከተሉት፡፡ወጥቶም ______________________አየና አዘነላቸው ______________________ ፈወሰ፡፡"

ሐ. ርህራሄ የእግዚአብሔር ማንነት መገለጫ ነው፡፡ በዘፀአት 34:6 ላይ እግዚአብሔር ስለራሱ ምን አለ? "የሚተኛበትም__________________ወደ እኔም ቢጮኽ __________________ ነኝና __________________::"

መ. ከኢየሱስ የምንማረው ነገር ርህራሄ ከሰው ከውስጥ ማንነት የሚወጣ እንጂ በውጫው ሁኔታ ተፅእኖ ስር እንዳልሆነ ነው፡፡ ልክ እንደማንነቱ ኢየሱስ ርህሩህ ነው፡፡ ኢየሱስ እየሞተ እያለ ለሚወዳት እናቱ እና ወዳጁ አሰበላቸው ወይንም እንክብካቤን አደረገላቸው፡፡ እርሱ ለእኛ የሚሰጠን የምሳሌ ህይወት ይህ ነው፡፡

## ትግበራ

ቅዱስ ጳውሎስ እኛም ለእግዚአብሔር ህዝብ እንድንራራ ያበረታታናል፡፡ በቆላስያስ 3:12 ላይ በእግዚአብሔር እንደተወደደ ህዝብ ምን እንድናደርግ ነው የምንበረታታው?

እንግዲህ እንደ _________________________________________________፤

_________________________________________________ ሆናችሁ፤

_________________________________________________ ሆናችሁ፥

_________________________________________________፤፥

_________________________________________________፤፥

_________________________________________________ ልበሱ፡፡

**ማስታወስ**

ቆላስያስ 3:12 በአዕምሯችሁ እንድታስውሱ ትበረታታላችሁ፡፡ በእርሱ አምሳያ የተፈጠርንበትን በደንብ እንድናስታውስ እንበረታታለን (ዘፍጥረት 1:27)፤ ለዓለም ማሳየት ያለብን የእርሱ መልክ እና አምሳያነት፡፡ በተለያየ ህመም እና ስቃይ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሲመለከት ኢየሱስ ራራላቸው፡፡ በጭንቀት ውስጥ ያሉትን ሰዎች በርህራሄ ስለተመለከተ የራሱን ፕሮግራም ተወና በፍቅር አገለገላቸው፡፡ የእርሱን ፍለጋ ተከትለን ሰዎችን በርህራሄ እንድንመለከትና በፍቅር እንድናገለግላቸው ምሳሌን ትቶልናል (1 ጴጥሮስ 2:21)፡፡

**ጥያቄ**

የራሴን የግል ምቾትን የግል አጀንዳ ወደ ጎን ትቼ ሰዎችን ሁሉ በርህራሄ ብመለከታቸው ህይወቴ ምን ሊመስል ይችላል?

________________________________________________________________________

**ፀሎት**

ርህራሄ የእግዚአብሔር ብቸኛ ልጅ የኢየሱስ ባህሪይ ነው፡፡ ጌታን ከጠየቃችሁት እርሱ በርህራሄ ይሞላችኋል፡፡ ለሌሎች የርህራሄን ልብ እንዲሰጣችሁ ጠይቁት፡፡ ሰዎች መረዳት በአለባቸው ጊዜ የራሳችሁን ጉዳይ ወደ ጎን በመተው በርህራሄ መርዳት እና ማገልገል እንድትችሉ እንዲረዳችሁ ጌታን በፀሎት ጠይቁ፡፡

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

# ትምህርት ሁለት

# አምላኬ፤ አምላኬ

## ከአራቱ ወንጌላት የተወሰዱ ምንባቦች - የተተወ

### የትምህርት ሁለት ምልከታ

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 2: ማርቆስ 11:1-11

- ኢየሱስ፤ የተተወ ልጅ
- *ተተለስታይ* ! ተፈፀመ!
- የኢየሱስ መቀበር
- በእለቱ ማሰላሰል
- በመቃብር ውስጥ እያለ ታተመበት

## መግቢያ

ለኢየሱስ ከተቀበለው መከራዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ከባዱ የእርሱ አባት እርሱን መተው ነበር። የእግዚአብሔር ቁጣ በልጁ በኢየሱስ ላይ ሆነ ለዚህም ነው አንዲያ ልጁ "አምላኬ፤ አምላኬ ለምን ተውከኝ?" ብሎ እንዲጮህ ያደረገው። እነዚህ ቃላት በአራት ዘዳግም ላይ እግዚአብሔር ለእስራኤል "አልተውህም ፤ አልለቅህም" ብሎ የተናገረው ጥልቅ እና አዲስ መረዳትን ያገኘበት ነው። ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት፤ "እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" በማለት ተናግሯል። ኢየሱስ እጅግ ከባድ መከራን ተቀብሎ ለእኔ ሞተ! ኢየሱስ ለእኔ ስለሞተ ከእርሱ የተነሳ ማንም ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየኝ አይችልም (ሮሜ 8:38-39)።
ለሶስት ሰዓቶች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዳለ ነው፤ ሁሉም ነገር ፀጥ ብሏል። ሁኔታውን ለመመልከት በዚያ የተሰበሰበው ህዝብ መበታተን ጀምሯል። በኢየሩሳሌም ህዝቡ ለፋሲካ በዓል ዝግጅት ሲያደርግ ሁለት ወንጀለኞች እና ምንም ጥፋት የሌለበት የእግዚአብሔር በግ በአሰቃቂ ሁኔታ ተሰቅለው ሲያጣጥሩ እየተመለከቱ ነበር።

በጥንቃቄ አድምጡ። በዚያ በኩል የምታፉ ከሆነ አንድ ጊዜ ቁሙ። እርሱ ውሃ እየጠየቀ ነው። እርሱ የሚፈልገው ነገር እንዳለ ያስታውቃል...

# ትምህርት 2

## <u>ምዕራፍ 1</u>

### *መግቢያ*

በማርቆስ 15:33 ላይ እንደዚህ ተብሎ ተፅፏል፤ ______________ ሰዓትም በሆነ ጊዜ፥ እስከ ______________ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ______________ ሆነ። ይህ ጨለማ የቆየው ______________ ሰዓታት ነው፤ ወይም እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ነው። በዚህ ምድር ሁሉ ጨለማ በሆነበት ጊዜ ኢየሱስ ስለተናገራቸው ነገሮች በንጌላት ውስጥ የተዘገበ ነገር የለም። ሉቃስ 23:45 ምንድነው የሚናገረው? ________________________________________

**የቤት ስራ**: ማርቆስ 15:33-34 አንብቡት። "ስድስት ሰዓት በሆነ ጊዜ______________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________።"

**ማሰላሰል**:

1. አሁን ጊዜው ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል። ኢየሱስ ከእኛ ኃጢአት የተነሳ እግዚአብሔር አባቱ ትቶታል ። እርሱ የኃጢአትን ሙሉ ቅጣት እየተቀበለ ነው። እርሱ ለእኛ ሲል መከራን እየተቀበለ ነው። እግዚአብሔር አብ ትቶታል፤ ኢየሱስ ብቻውን ቀርቷል።
2. እኛን እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ አልተወንም። በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ክፍሎች እግዚአብሔር በፍፁም እንደማይተወን ይናገራሉ። በሚከተሉት ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔር የሚናገረን ነገር ምንድነው?

   ሀ.መዝሙር 27:9-10

   ______________________________________________________________

   ለ. መዝሙር 37:27-28ለ

   ______________________________________________________________

   ሐ. ኤርምያስ 14:9ለ

   ______________________________________________________________

   መ. ዕብራውያን 13:5ለ

   ______________________________________________________________

3. ህይወት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ያህል አንዳንድ ሰዎች ትዳራቸውን " ህያው መቃብር " ነው ይላሉ። ሌሎች ሰዎች ደግሞ ህይወታቸውን "በሲዖል ውስጥ እያለፍኩኝ" በማለት ይገልፁታል። ህይወት ከባድ እና አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ሰዎች በተደጋጋሚ፤ "በዚህ ሁሉ ስቃይ ውስጥ እግዚአብሔር የት ነው ብለው?" ይጠይቃሉ። አንዳንድ ሰዎች የሚቀበሉት መከራ የሚገባቸው አይደለም፤ ፍትሃዊም አይደለም። በህይወት ውስጥ ለሚደርስብን መከራ ሁሉ ከኃጢአት የተነሳ ነው። በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

____________________________________________________________

____________________________________________________________

4. ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተቀበለውን መከራ በቃላት መግለፅ አይቻልም ምክንያቱም ያ መከራ እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ያሳየው ቁጣው ስለሆነ ነው። ኢየሱስ የዓለም ኃጢአት ተሸከመ። ይህንን በእርሱ ፈንታ የሚሸከም ማንም የለም። እርሱ ሲሰቃይ እና ሲሞት ሊረዳው የሚችል ማንም የለም። ማንም እርሱን የሚተካ አልነበረም። እርሱ ብቻውን ለእኛ ሲል መከራን መቀበል ነበረበት። እግዚአብሔር ተወን ማለት እርሱ ፀሎታችንን አይሰማም ማለት ነው ብለን ማሰብ እንችላለን። እግዚአብሔር ተወን ማለት የምንወዳቸው ሁሉ ይሞታሉ ብለን ማሰብ እንችላለን ወይንም የምንወዳቸው ሲሞቱብን እግዚአብሔር ትቶናል ብለን ልንደመድም እንችላለን። እግዚአብሔር ተወን ማለት ስራ አናገኝም፤ ልጆቻችንን በአግባቡ እና በስርዓቱ ማሳደግ አንችልም፤ ልጅን መውለድ አንችልም፤ ወይም ጤና አይኖረንም ብለን ማሰብ እንችላለን። ኢየሱስ አምላኬ ለምን ተውከኝ ሲል ፍቅር የሆነው አባቱ በኃጢአት ላይ ከነበረው ቁጣ የተነሳ እርሱን ስለተወው ነው ። የእርሱ መከራ እና ሞት ከኃጢአት እና ከዲያብሎስ የተነሳ ነው። ኃጢአት ወደ ፍጥረት ሁሉ ስለገባ እኔ እና እናንተ መሞት አለብን።

5. *የእግዚአብሔር እቅድ፤ የእኛ ምርጫ* በሚለው ጥናት ውስጥ ዘፍጥረት 1-11 ስናጠና ዲያብሎስ አዳም እና ሔዋንን በእግዚአብሔር እና በእርሱ ቃል ላይ እንዲያምፁ እንዳደረጋቸው እና እንዳሳታቸው ተመልክተናል። ይህ ዓመፅ በእግዚአብሔር እና በእኛ መካከል የነበረውን ግንኙነት አበላሸ። ይህ የተበላሸው ግንኙነት ሊታደስ የሚችለው በእግዚአብሔር ሃይል ብቻ ነው። እኛ መከራ እና ሞትን ልንቀበል የተገባን ነን ነገር ግን ኢየሱስ ህይወት እና ድነት ሊሰጠን ፈለገ። የኢየሱስ ስራ ለእኛ የተገባውን ቅጣት እርሱ ተቀበለ። በእኛ ምትክ እንዲሞት እግዚአብሔር የእርሱ አንድ ልጅ ኢየሱስ አሳልፎ ሰጠ። የሚከተለው ጥቅስ ይህንን በደንብ ይገልፃል: "የኃጢአት ደመወዝ ____________________ ነውና፤ ____________________ የጸጋ __________ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ____________________ ነው። (ሮሜ 6:23)።"

የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

6. ስለ ካህናት አለቆች እና ባለስልጣኖቻቸው በዚህ ስፍራ ብዙ የተባለ አለመኖሩ የሚገርም ነው፡፡ የስቅለቱን ስፍራ ለቅቀው ሄዱ? ማድረግ የፈለጉትን ነገር አደረጉ? ኢየሱስ ከተሰቀለ በኂላ ስድባቸውን እና ጭኸታቸውን ከአሰሙ በኂላ ያሰብነው ልተሳክቷ ብለው ወደ ቤታቸው ሄዱ? የኢየሱስ መሞት ሰዓታትን ይፈጃል፡፡ ስለእነርሱ የምናውቀው ነገር ወደ ጵላጦስ ቀርበው በኢየሱስ መስቀል ላይ ጵላጦስ ፅፎ ስለሰቀለው ፅሁፍ እንዳልተስማሙ አቤቱታ ሲያቀርቡ ነው፡፡ ፅሁፉም "የናዝሬቱ ኢየሱስ፤ የአይሁድ ንጉስ" ይላል፡፡ ተቃዋሚዎቹ ጵላጦስ ምን ብሎ እንድፅፍ ነው ግድ ያሉት (ዮሐንስ 19:21)?

______________________________________________________________________________

የአይሁድ አለቆች እውነትን ሊያዛቡ ፈለጉ ነገር ግን አሁን ጵላጦስ እነርሱን መስማት በቅቶታል፡፡ ምናልባት ጵላጦስ ስልጣኑን ተጠቅሞ በኢየሱስ ክስ ወቅት ትክክለኛ ውሳኔን መወሰን አለመቻሉ አሳዝኖት ይሆናል፡፡ ለሰዎቹ ጥያቄ የጵላጦስ ምላሽ ምንድነው (ቁጥር 22)?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

<u>ምዕራፍ 2</u>

*መግቢያ*

አሁን ሰዓቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆኗል፡፡ ኢየሱስ ነፍሱን ለአባቱ አሳልፎ ሊሰጥ ነው፡፡ እርሱ ስራውን ስላጠናቀቀ ከመሞቱ በፊት ኢየሱስ የሆነ ነገር ሊናገር ነው፡፡

**የቤት ስራ**: ዮሐንስ 19:28-30 አንብቡት፡፡

**መልመጃ**:

1. በዮሐንስ 13:1 ኢየሱስ ይህንን ዓለም ትቶ የሚሄድበት ጊዜ እንደደረሰ እንዳወቀ ይነገራል፡፡ ኢየሱስ ምንድነው ነው ያወቀው (ቁጥር 28ሀ)?

   ____________________________________________________________

2. ሁሉም ነገር ተፈፅሟል፡፡ እርሱ እንዲያደርገው አባቱ የሰጠውን ስራ ኢየሱስ ፈፅሟል፡፡ ነገር ግን በቅዱሳት መፃህፍት የተፃፈው ሁሉ መፈፀም አለበት፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ ምን አለ?

   ______________________________________________________________________________

3. ያለጥርጥር ኢየሱስ ውሃ ፈልጓል፡፡ ለዘጠኝ ሰዓታት ምንም ነገር አልጠጣም፡፡ አንድ ሰው አፉ ከደረቀ መናገር ይቸግረዋል፡፡ ኢየሱስ "ተጠማሁ" አለ፡፡ ይሁን እንጂ ዓለም ሁሉ መስማት ያለበትን አንድ ቃል መናገር አለበት፡፡ በውሃ ጥም ደርቆ የተሰነጣጠቀው አፉ የተቀበለው ሆምጣጤን ነው፡፡ ኢየሱስ ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ ምን አለ (ቁጥር 30 31)?

________________________________________________________

ይህ ዓረፍተ ነገር በግሪክ ቋንቋ "*ተተለስታይ*" *ይባላል* ፡፡ ይህ ቃል የሚያሳየው በጊዜ እና በዘላለማዊነት ውስጥ እጅግ ታላቅ የሆነ ተግባር ተከናወነ፤ ስራ ተፈፀመ ማለት ነው፡፡ ለእኛ ድነት ከዚህ በላይ የሚሰራ ስራ የለም፡፡ *ተተለስታይ!*

4. ሴቶቹ ብቻ ሳይሆኑ፤በመስቀሉ ዙሪያ የተሰባሰቡት ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ ወታደሮቹ ብቻ ሳይሆኑ ፤ ጵላጦስ ብቻውን ሳይሆን፤ሐና እና ቀያፋ ብቻ ሳይሆኑ፤ የካህናት አለቆች እና አይሁድ መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ሰው እየሰማው ኢየሱስ "*ተተለስታይ!*" ማለት ፈልጓል፡፡ የእርሱ ደቀ መዛሙርት ሁሉ የትም ቢሆኑ በሁሉም ቦታ የሚገኙ ሳምራውያን እና ህዝቦች፤ብሔር ብሔረሰቦች ሁሉ ይህንን ቃል እንዲሰሙ ኢየሱስ ፈልጓል፡፡ በቅርብ እና በሩቅ ያሉ፤ በመላው ዓለም ያለው ህዝብ ሁሉ "*ተተለስታይ!*" ብሎ ሲናገር እንዲሰሙ ኢየሱስ ፈልጓል፡፡ እኔ እና እናንተ፤ የእኛ ጎረቤቶች እና ጓደኞች፤ አብረውን የሚሰሩ ሰዎች ሁሉ፤ የመንግስት ባለስልጣናት ሁሉ ኢየሱስ "*ተተለስታይ!*" ሲል እንዲሰሙት እርሱ ይፈልጋል፡፡
5. በሉቃስ 23:46 ላይ ምን ሆነ "_________________________________________________________________________________________________________________፡፡"
6. ኢየሱስ ሄሮድስ፤ ከዚያም ለጵላጦስ፤ እንዲሁም ለህዝቡ ተላልፎ ተሰጠ፡፡ አሁን ደግሞ እርሱ ራሱን አሳልፎ ለአባቱ ሰጠ፤ እንዲህም አለ " ______________ በእጅህ አደራ አሳልፌ እሰጣለሁ፡፡" ከዚያም ኢየሱስ የመጨረሻውን ትንፋሽ ተነፈሰ፡፡ አንገቱን አጎንብሶ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ፡፡ የወንጌላት ፀሃፊዎች ኢየሱስ የኃጢአት፤ የሞት፤ እና የዲያብሎስ ተጠቂ ሆኖ ሞተ አላሉንም፡፡ ይልቁንም ኢየሱስ በፅድቅ ለሚፈርደው አባቱ ራሱን አሳልፎ ሰጠ (1 ጴጥሮስ 2:23ለ)፡፡ "ነገር ግን ____________________________________________፡፡"

**ማሰላሰል**

*ተፈፀመ ፤"ተተለስታይ!" የሚለውን ቃል በሚገባ ከአሰላሰላችሁ በኋላ ስለዚህ ነገር የተረዳችሁትን ፃፉ፤*

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

__________________________________________________________

**ማሰላሰል**

ኢየሱስ እንድትሰሙት የሚፈልገውን ቃል እና የእናንተ ምላሽ ምን እንደሆነ በማሰላሰል ፃፉ:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ምዕራፍ 3**

**መልመጃ**: ኢየሱስ ሲሞት ከዚያ በፊት ሆኖ የማያውቅ ተዓምር ሆነ።

1. ማቴዎስ 27:51-52 የሚነግረን ነገር ምንድነው?

   ሀ.____________________________________________________________

   ለ.____________________________________________________________

   ሐ.____________________________________________________________

   መ.____________________________________________________________

   ሠ.____________________________________________________________

2. የመቶ አለቃው እና አብረውት የሚጠብቁት ወታደሮች ሁኔታ እንዴት ነበር? ስለተመለከቱት እና ስለሰሙት ነገር ምን አሉ (ማቴዎስ 27:54፤ ሉቃስ 23:47)?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

3. ስለተመለከቱት እና ስለሰሙት ነገር የሴቶች ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 55)?

   ____________________________________________________________

4. ሁኔታው ለመመልከት የተሰበሰቡት ሰዎች ምላሽ ምን ነበር (ሉቃስ 23:48)

   ______________________________

5. ኢየሱስ የሞተበት ቀን ለፋሲካ በዓል የዝግጅት ቀን ነበር። የሚቀጥለው ቀን ደግሞ ልዩ የሆነ የፋሲካ በዓል የሚከበርበት ነው። ለአይሁድ ይህ የፋሲካ በምንድነው ለየት ያለው (ዮሐንስ 19:31)?____________________________________________________

   ____________________________________________________________

6. ጲላጦስ ወታደሮቹ ምን እንዲያደርጉ ነው ያዘዛቸው (ቁጥር 32)?

   ____________________________________________________________

   ____________________________________________________________

7. ወታደሮቹ የኢየሱስ አካል ምን አደረጉ (ቁጥር 33)?

   ____________________________________________________________

______________________________________________________________________

8. ኢየሱስ በትክክል ሙቷል ወይስ አልሞተም የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ነው። በቁጥር 34 ላይ የምንመለከተው ነገር ወታደሮቹ አንዱ የኢየሱስን ጎን በጦር በወጋው ጊዜ "ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።" በሞት ጊዜ በልብ አካባቢ የሚገኘው ፈሻስ ደም እና ውሃን ይመስላል። እንደ ቁጥር 35 አገላለፅ ይህ ሲሆን የተመለከተው ማነው? ይህንን እንዴት አወቃችሁት?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

9. የኢየሱስ አስክሬን እንዲሰጠው የጠየቀው ማነው (ቁጥር 38)?

______________________________________________

10. ስለዮሴፍ የምናውቀው ነገር ምንድነው ዮሴፍ (ቁጥር 38፤ ሉቃስ 23:50-51)

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

11. ከእርሱ ጋር ማን ነበረ? ኒቆዲሞስ በሌሊት መጥቶ ኢየሱስን ስለጎበኘበት ሁኔታ ምን የምታስታውሱት ነገር አለ (ዮሐንስ 3)? ኢየሱስ ምን ጠየቀው?

_____________________________________________________________________

_____________________________________________________________________

12. ኒቆዲሞስ ምንድነው ይዞ የመጣው (ቁጥር 39)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

እነዚህ ሰዎች ምን ሊያደርጉ ነው (ቁጥር 40)? __________________________________

______________________________________________________________________

13. ሰዎቹ ቸኩለዋል። ቀኑ የአይሁድ የዝግጅት ቀን ነበር። መቃብሩ የሚገኝበት ስፍራ የት ነው (ቁጥር 41-42)?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

14. የእርሱ መቃብርን ልዩ የሚያደርገው ነገር ምንድነው (ቁጥር 41)

____________________________________________

15. ከማርቆስ 15:43-45 ላይ የምናገኘው ተጨማሪ ነገር ምንድነው? _____________________

______________________________________________________________________

16. ከርቀት ሆነው የሚመለከቱት እነማን ናቸው?

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**<u>ምዕራፍ 4</u>**

**ማሰላሰል**:

1. ከእነዚህ ሰዎች መካከል የእናንተ ባህሪይ ከየትኛው ጋር ይመሳሰላል? ራሳችሁን የቱ ጋ አገኛችሁት? የመቶ አለቃው በሆነው ነገር እጅግ ተደንቋል። የሚሆነውን ሁሉ ሴቶች ከርቀት ይመለከቱ ነበር። ከዮሐንስ በስተቀር የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ሁሉ የት እንዳሉ አይታወቅም ። የአርማቴሱ ዮሴፍ ጵላጦስን የኢየሱስን አስክሬን እንዲሰጠው ጠየቀ። ኒቆዲሞስ ደግሞ ኢየሱስን በመገነዝ አርማቴሱ ዮሴፍን አገዘው። መግደላዊት ማርያም አዳኟዋ በመሞቱ እጅግ አዝናለች፤ ጌታዋ እንዴት እንደሚቀበር ለማየት ከመቃብሩ አካባቢ አልተለየችም ። በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

2. የህዝቡ ሁካታ እና ጩኸት አሁን የለም። አሁን ማንም በኢየሱስ ላይ የሚጮህና የሚሳደብ የለም። ሶስቱም የተሰቀሉት ሰዎች ሙተዋል። ታላቁ ክንዋኔ አሁን አብቅቷል። ዮሴፍ እና ኒቆዲሞስ በፍቅር የኢየሱስ አስክሬን ከመስቀል ላይ አውርደዋል። የእርሱ አካል በደረቀ ደም ተልውሷል፤ተበሳስቷል ። አሁን ሁሉም ነገር ፀጥ ብሏል። ሁሉም ሰው ለፋሲካ በዓል ዝግጅት ወደ ቤቱ ሄዷል። የእናንተ ሃሳቦች:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

3. ከዚያ ሁሉ ሁከት እና ጫጫታ በኋላ የኢየሱስ ሞት ሰላምን አምጥቷል። ስርዓት አልበኝነቱ አብቅቶ አሁን ሁሉም ነገር ፀጥ ብሏል። ፀጥ ያለው ኢየሱስ የተሰቀለበት ኮርብታ አካባቢ እና የመቃብሩ ስፍራ ብቻ ሳይሆን የእርሱ ተከታዮች ልብም ጭምር ነው። ፀጥታው ሰላማዊ ነበር? ምን ሆን? ከሳምንት በፊት እየጮሁ እና እየዘመሩ አጅበውት ኢየሩሳሌም ያስገቡት ሰው ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ እንደዚያ ተሰቃይቶ ተሰቅሎ ይሞታል እንዲሁም ይቀበራል ብሎ ለማመን ማንም አይችልም። ሁሉም ነገር ተገለባብጦባቸዋል። የእነርሱ መሪ፤አስተማሪና አለቃ አሁን ሙቷል። ይህንን ማመን እጅግ ይከብዳል። ሁሉም ሰው አሁን በኪሳራ ውስጥ ነው ያለው። አይደለም እንዴ? የመቶ አለቃውና ጠባቂ ወታደሮቹ ሃሳባቸው የቀየሩ ይመስላሉ። ማቴዎስ 27:54 ላይ እነርሱ ምን አሉ?

______________________________________________________________________

ስለዚህ ነገር የእናንተ ሃሳብ ምንድነው:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ምዕራፍ 5**

**መልመጃ**:

1. የካህናት አለቆች እና ፈሪሳውያን ያሳሰባቸውን ነገር ለ _______________ የተናገሩት (ማቴዎስ 27:62)፡፡

   ሀ. እነርሱ ኢየሱስን ለመግለፅ የተጠቀሙበት ቃል ምንድነው (ቁጥር 63)?

   ______________________________

   ለ. ኢየሱስ ምን ብሎ የተናገረው ነገር እነርሱን ያሳሰባቸው (ቁጥር 63ለ)?

   ______________________________

   ሐ. የእነርሱ ጥያቄ ምን ነበር (ቁጥር 64)?

   ______________________________

   ______________________________

   መ. ይፈጠራል ብለው የፈሩት ነገር ምንድነው (ቁጥር 64ለ)?

   ______________________________

   ______________________________

2. የጵላጦስ ትዕዛዝ ምን ነበር (ቁጥር 65)?

   ______________________________

3. ጠባቂዎቹ ምን ሊያደርጉ ነው (ቁጥር 66)?

   ______________________________

   ______________________________

   በጵላጦስ እይታ መሰረት ሁሉም ሰው በአስተማማኝ ጥበቃ እና ሰላም ውስጥ ነው ያለው፡፡ የካህናት አለቆች እና ሌሎች ባለስልጣናት የፋሲካን በዓል በሰላም ለማክበር ማድረግ የሚገባችውን ሁሉ አድርገዋል፡፡ መቃብሩ ታትሞበት ታሽጓል! ጠባቂዎች በቦታው ተሰማርተዋል፡፡

**ትግበራ**

አንድ ማሰብ ያለብን ጉዳይ አለ… እኔ ሰላም እና መረጋጋት የሚሰማኝ ኢየሱስ ሞቶ በመቃብር ውስጥ ተቀብሮ ታሽጎበት እያለ ነው ወይስ በህይወት እያለ ሰዎችን ሲያገለግል፤ ሲያስተምራቸው እና እርሱን እንድከተል ሲጋብዘኝ ነው?

______________________________

______________________________

**ማስታወስ**:

ይህ አስቸጋሪ እና ከባድ ጥያቄ ነው ነገር ግን ጊዜ ወስዳችሁ የኢየሱስን ሰባት አረፍተ ነገሮች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ በመፃፍ የምዕራፍ 5 ትምህርትን በደንብ ለመረዳት ሁለት አረፍተ ነገሮችን እንድትፅፉ ትበረታታላችሁ። በደንብ ለማስታወስ እንድትችሉ ወደኋላ ሄዳችሁ እስካሁን ድረስ የተማራችሁትን መከለስ ትችላላችሁ።

1. አባት ሆይ

   ______________________________________________

2. ዛሬ

   ______________________________________________

3. አንቺ ሴት

   ______________________________________________

4. አምላኬ፤

   ______________________________________________

5. እኔ______________________________________________

6. ______________________________________________

   *ተተለስታይ*!

7. አባት ሆይ፤

   ______________________________________________

**ፀሎት**

**ስትፀልዩ እነዚህን** የኢየሱስን አባባሎች በፀሎታችሁ ውስጥ አካትቱ። ለምሳሌ ጠላቶቻችሁን እግዚአብሔር ይቅር እንዲል ጠይቁት። የሆነ ሰውን ከኢየሱስ ጋር አገናኙታችሁ፤ ከኢየሱስ ዛሬ ከእኔ በገነት ትሆናለህ/ሽ የሚለውን ቃል እንዲሰሙ ማድረግ እንድትችሉ ጌታ እንዲረዳችሁ። ይህንን ምሳሌ በመከተል በሌሎችም የኢየሱስ አባባሎች በዚህ መልክ በፀሎታችሁ ውስጥ እያስገባችሁ ፀልዩ።

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

# ትምህርት ሶስት

# ሂዱና ተናገሩ!

## ከአራቱ ወንጌላት የተወሰዱ ምንባቦች — እርሱ ተነስቷል!

---

**የትምህርት ሶስት ምልከታ**

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 3: ከአራቱ ወንጌላት የተወሰዱ ምንባቦች

- ትንሳኤ፤ የመሬት መንቀጥቀጥ
- ኑና እዩ
- ስለትንሳኤ ማሰላሰል
- አትፍሩ
- ይቅር ተባለ
- ሂዱና ተናገሩ

## መግቢያ

የመስቀሉ ሰቆቃ አሁን አብቅቷል፡፡ የፋሲካ በዓል ተከብሮ አልፏል፡፡ ዛሬ እለቱ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ነው፡፡ ጠባቂዎች መቃብሩን መጠበቃቸውን ቀጥለውበታል፡፡ የአይሁድ ንጉስ ነኝ ያለው ሰው ሙቷል፡፡ ያለፉት ቀናት ሁካታና ደስታ አሁን አብቅቷል፡፡ አሁን በኢየሩሳሌም ሰላም ሰፍኗል፡፡ ወይስ ሰላም ይመስላል፡፡ ቢያንስ ጵላጦስ፤ ቀያፋ፤ ሐና እና የህዝቡ ሽማግሌዎች በዚህ መልኩ ነው ያሰቡት፡፡ በእነርሱ አመለካከት በህዝቡ ዘንድ ሁከትን የፈጠረው ሰው አሁን የለም፡፡

በትምህርት ሶስት ውስጥ የቀረቡ የተለያዩ ነጥቦች አሉ፡፡ በአትኩሮት ተመልከቷቸው፡፡ የመልአኩን ግብዣና እና ትዕዛዝ ትኩረት ሰጥታችሁ አድምጡት፡፡ ኢየሱስ ሴቶቹን የተናገራቸውን ነገር አድምጡ፡፡ የኢየሱስን ትንሳኤ አስመልክቶ የእናንተ ምላሽ ምንድነው፡፡ የእርሱ ትንሳኤ በእኔ ህይወት ውስጥ ያመጣው ለውጥ ምንድነው? ለእኔ የእርሱ ግብዣ ምንድነው? ምን እንዳደርግ ነው እርሱ እኔን የሚጋብዘኝ እና ሃይልን የሚሰጠኝ?

በአስቸኳይ ሂዱና ተናገሩ! እንደተናገረው እርሱ ተነስቷል!

# ትምህርት 3

## ምዕራፍ 1

### መግቢያ

የፋሲካ ቀን መጥቷል። ለአይሁድ ይህ የሳምንቱ ቀን የአምልኮና የእረፍት ቀን ነው። በበዓሉ ላይ በዋናነት ሰዎች ሁሉ በየቤታቸው የሚወያዩበት ርዕስ በኢየሩሳሌም ከተማ ከበዓሉ አንድ ቀን ቀደም ብሎ የሆነው ታላቅ ክንውን ነው። ኢየሱስ ተሰቅሏል ደግሞም ሙቷል! ለተወሰኑ ሰዎች ይህ ክስተት ሊቀበሉት የማይችሉት እና ሃዘናቸውም ከአቅማቸው በላይ ሆኖባቸዋል። ለሌሎች ደግሞ እራሱን የአይሁድ ንጉስና የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ያለውን ኢየሱስ በመጨረሻ ላይ በመሞቱ ከመንገድ ላይ በመወገዱ እፎይታ ተሰምቷቸዋል። የኢየሱስ የቅርብ ወዳጆች እና አብረውት የነበሩት ሁሉ ቀጥለው የሚገደሉት እነርሱ መሆናቸውን በማሰብ በፍርሃት ተውጠው በሮቻቸውን ዘግተው በድብቅ ተቀምጠዋል (ዮሐንስ 20:19)።

**የቤት ስራ**: *ማቴዎስ* 28:1-10 አንብቡት። የዚህ ታሪክ ተጨማሪ ሃሳቦች በማርቆስ 16:1-8፣ በሉቃስ 24:1-10፣ እና ዮሐንስ 20:1-9 ላይ ይገኛል። እነዚህን አራቱንም የንባብ ክፍሎች እንድታነቡ ትበረታታላችሁ። እያንዳንዱ የንባብ ክፍል የራሳቸው የሆነ ትኩረት የሚሰጡበት ነጥብ አላቸው።

**መልመጃ**: *ማቴዎስ* 28:1-10

1. እለቱ የሳምንቱ ስንተኛ ቀን ነበር (ቁጥር 1)?

   ________________________________________

2. ድርጊቱ በስንተኛው ሰዓት ነበር የተከናወነው?

   ______________________________________________

3. ወደ መቃብሩ የመጣው ማነው?

   ______________________________________________

   አራቱም ወንጌላት መግደላዊት ማርያም ወደ መቃብሩ እንደመጣች ዘግበዋል። ሁለቱ ወንጌላት ደግሞ የያዕቆብ እናት ማርያም ወደ መቃብሩ እንደመጣች ገልፀዋል ። አንዱ የወንጌል ፀሐፊ ሰሎሜን ሲጠቅሳት ሌላኛው ደግሞ ዩሐና ወደ መቃብሩ እንደመጣች ዘግበዋል። ከመግደላዊት ማርያም በቀር ስለሌሎቹ ሴቶች ብዙም የምናውቀው ነገር የለም። አንድ የምናውቀው ነገር እነዚህ ሴቶች ኢየሱስን ሲከተሉት፣ በሚያስፈልገውም ነገር ሲያገለግሉትና ሲሞትም በአጠገቡ ነበሩ (ማቴዎስ 27:55-56)። አሁን ሌሊቱ እየነጋ ነው እነርሱም "ሰንበትም ካለፈ በኋላ

____________________የያዕቆብም እናት ማርያም ____________________ መጥተው ሊቀቡት ____________________ ገዙ።” (ማርቆስ 16:1)።

4. በአዕምሮአቸው ስለነበረው ትልቅ ጥያቄ ማርቆስ የሚነግረን ነገር ምንድነው (ቁጥር 3)?

________________________________________

________________________________________

5. እንደ ማቴዎስ 28:2ሀ ዘገባ መሰረት እነዚህ ሴቶች ወደ መቃብሩ ሲቀርቡ ምን ሆነ?

________________________________________

6. መልዓኩ ምን አደረገ (ቁጥር 2ለ)?

________________________________________

7. ቁጥር 3 መልአኩ ምን ይመስላል ብሎ ይዘግባል:

________________________________________

8. በጠማቂዎቹስ ምን ሆኑ (ቁጥር 4)?

________________________________________

________________________________________

9. ለሴቶቹ መልአኩ ምን አላቸው?

ሀ.ቁጥር 5ሀ:

________________________________________

ለ. ቁጥር 5ለ:

________________________________________

ሐ. ቁጥር 6ሀ:

________________________________________

መ. ቁጥር 6ለ:

________________________________________

10. በቁጥር 7ሀ ላይ የተሰጣቸው ትዕዛዝ ምንድነው?

________________________________________

11. ለደቀ መዛሙርቱ የነበረው መልዕክት ምንድነው?

________________________________________

________________________________________

12. ሴቶቹ ከመቃብሩ ፈጥነው ሲሄዱ የተሰማቸው ስሜት ምን ነበር (ቁጥር 8)?

________________________________________

13. በቁጥር 8 ላይ የእነርሱን ደስታና እና ፍጥነት ለመግለፅ የተጠቀሱ ሁለት ቃላት የትኞቹ ናቸው?

_______________________________ እና ___________________________________

14. በመንገዳቸው ላይ የተገናኛቸው ማነው (ቁጥር 9)? ___________________

15. “እነሆም፥______________________አገኛቸውና፡፡___________________ይበላችሁ አላቸው፡፡ እነርሱም ቀርበው______________________ይዘው ______________________፡፡”

16. ኢየሱስ የተናገራቸው ነገር ምንድነው (ቁጥር 10)?

ሀ.________________________________________________________

ለ.________________________________________________________

ሐ.______________________________________________________ (ማቴዎስ 28:16)

**ምዕራፍ 2**

**ማሰላሰል**:

1. ስለትንሳኤው ታሪክ የተረዳችሁት ነገር ምንድነው?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

የእናንተን ትኩረት የያዘው የቱ ነው?

___________________________________________________________________________

___________________________________________________________________________

2. የፋሲካው ቀን ለእነዚህ ሴቶች ከባድ ነበር፡፡ በአይሁድ ስርዓት መሰረት በዚህን ቀን ምንም ዓይነት ስራ መስራት ስለማይፈቀድ እነዚህ ሴቶች ለኢየሱስ መቃብር አስፈላጊውን ነገር ለማድረግ የሳምንቱን መጀመሪያ ቀን መጠበቅ ነበረባቸው፡፡ የኢየሱስ ቀብር የተከናወነው በችኮላ ነበር ምክንያቱም የፋሲካ ቀን ከመግባቱ በፊት ፈጥነው መስራት የሚገባቸውን ስራ ማከናወን ስለነበረባቸው ነው፡፡ እነዚህ ሴቶች በከባድ ሃዘን እንደተመጡ መገመት ይቻላል፡፡ አንዳንዶቹ ሴቶች ከኢየሩሳሌም በስተሰሜን ከምትገኘው ገሊላ ጀምሮ ተከትለውታል፡፡ እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካ እራት ከበላ በኂላ ቀጥሎ ሊታመን የማይችል ነገር ሆነ፡፡ እርሱ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሙቷል፡፡ ምንድነው የተፈጠረው ችግር? ይህንን ውጥንቅጥ የበዛበትን የእብደት ነገር እንዲሆን ያደረገው ምንድነው? ሁሉም ሰው እየተንጫጫ ይጮሃል፡፡ ህዝቡ ከቁጥጥር ውጭ ሁኗል፡፡ ይህ ሁሉ በድንገት አበቃ፡፡ እርሱ ሙቷል፡፡ በዚህን ጊዜ ነበር ያልተለመደ ነገር መሆን የጀመረው፡፡ የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከታች ተቀደደ፡፡ መሬት ተንቀጠቀጠች፤ ድንጋዮች ደግሞ ተሰነጣጠቁ፡፡ መቃብሮች ተከፈቱና ከዚህ በፊት ሞተው የነበሩ በርካታ ቅዱሳን ሰዎች ከመቃብር በህይወት ተነሱ (ማቴዎስ 27:51-52)፡፡ እናንተ

በፋሲካ እለት በቤታችሁ ሆናችሁ ከፋሲካው ቀን ቀደም ብሎ በኢየሱስ ላይ የደረሰበትን ሁሉ ስታስቡት የሚሰማችሁ ስሜት ምን ሊሆን ይችላል? በዚህ ላይ የእናንተ አስተያየት ምንድነው?

________________________________________________

________________________________________________

3. ለዘላለሙ ታሪክን የሚለውጥን ድርጊት በድንገት እግዚአብሔር ጀመረ! ፍጥረት ትንሳኤውን አወጀ! ሃይለኛ የመሬት መንቀጥቀጥ ምድርን አናወጠ! ስለመሬት መንቀጥቀጥ ፣ ስለመልአኩ መምጣት፣ ወደ መቃብር መሄድ እና ስለድንጋዩ መንከባለል የዘገበው ማቴዎስ ብቻ ነው። ማነው የመሬት መንቀጥቀጡን የተሰማው? ሌሎች ፀሐፊዎች ምን አሉ?

   ሀ. ማርቆስ 16:1-4

   ____________________________________________

   ለ. ሉቃስ 24:1-3

   ____________________________________________

   ሐ. ዮሐንስ 20:1

   ____________________________________________

ማቴዎስ የመልአኩን መገለጥ ገልፆ ፅፏል። ይህ ሁሉ በሆነ ጊዜ ጠባቂዎቹ እጅግ ፈርተው ነበር "ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ። (ቁጥር 4)።" በዚህ ላይ ያላችሁን አስተያየት ግለፁ:

________________________________________________

________________________________________________

## <u>ምዕራፍ 3</u>

**ማሰላሰል** (የቀጠለ):

4. **መልአኩ** በድንጋዩ ላይ ተቀምጧል። ይህንን ነገር ስታስቡ የሚያስደንቅ ሃሳብ ወደ አዕምሮአችሁ ሊመጣ ይችላል። መልአኩ ወደ መቃብሩ ጎብኚዎች እንደሚመጡ ገምቶ ሊሆን ይችላል። እርሱ እጅግ በጣም ታላቅ የሆነ ዜናን ማለትም ኢየሱስ እንደተናገረው እንዲሁ ከሞት መነሳቱን ለዓለም ሁሉ በማወጁ በጣም ደስተኛ እና እድለኛ ሆኗል። ጠባቂዎቹ ፈርተው እንደሞተ ሰው ሆነው በመሬት ላይ ሲወድቁ መልአኩ ፈገግ ቢል አንድ የሚያስደንቅ ነገር ። እነዚህ ሰዎች መቃብር ከዘራፊዎች ማለትም ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለመጠበቅ የተላኩ አይደለም እንዴ? ታላቅ መንቀጥቀጥ፣ የመልአኩ መገለጥ፣ የድንጋዩ መንከባለል እና የጠባቂዎቹ ለመጠበቅ ሃይል ማጣት እና እንደሞተ ሰው ሆነው መተኛታቸው ይህ ሁሉ እጅግ አስደናቂ ታሪክ ነው። መቃብሩ ተከፍቷል፣ ተጋልጧል፣ ባዶ ነው፣ አሁን ለጎብኚዎች እራሱን ባዶ አድርጓል!

5. መልአኩ ለሴቶች የተናገራቸው የመጀመሪያዎቹ ቃላት፤"_____________________________" ናቸው። ሴቶች የመጡት የተቀለውን የጌታቸውን አስክሬን ፈልገው እንደሆነ አውቋል። የእርሱ አስክሬን ወደ መቃብር በዮሴፍ እና በኒቆዲሞስ እንደተቀመጠ ከተመለከቱ ጊዜ አንስተው ይህንን ለማድረግ እያሰቡ ነበር። አሁን ግን የገጠማቸው እንደመብረቅ የሚያንፀባርቅ ብርሃን፤ እንደ በረዶ የነጣ ልብሶች እና "አትፍሩ" የሚልን ድምፅ ነው። ከዚያም መልአኩ ለሴቶቹ የሚፈልጉት ጌታ በዚያ እንደሌለ ተናገራቸው። መልአኩ ይህንን የተናገረው ለእናንተ ቢሆን ኖሮ ይህንን ስትሰሙ ወዲያውኑ ምን ታደርጉ ነበር? ምናባትም "ማን ነው የወሰደው?" ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። መልአኩ የነገራቸው ታላቅ የምስራችን ነው: "እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም።"

6. መልአኩ ሴቶችን በቆሙበት እንዲቀሩ አላደረገም ነገር ግን ወደ መቃብሩ እንዲመጡ እና መቃብሩ ባዶ መሆኑን እንዲመለከቱ ጋበዛቸው። ከዚያም ለሴቶቹ መመሪያን ሰጠ። እነርሱ ምን ማድረግ አለባቸው (ቁጥር 7)?

_______________________________________________________________

7. ለደቀ መዛሙርት የሚነግሩት መልዕክት ምንድነው?

_______________________________________________________________

_______________________________________________________________

ደቀ መዛሙርቱ ምንም እንኳን ከሁሉም ቀድመው ወደ መቃብሩ የደረሱ ባይሆኑም፤ የእነርሱ ትኩረት ኢየሱስ ከሞት መነሳቱን ለማወቅ ነው። "ፈጥናችሁም ሂዱና። ከሙታን ተነሣ፥… ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው።" ይህንን የምስራች ለመናገር መጣደፍ አለ!

8. ከዚያም ሴቶቹ በተቀላቀለ ስሜት ውስጥ ሆነው እየተጣደፉ ሄዱ። ምንም እንኳን የፈሩ ቢሆኑም ደስታው አስገድዷቸው ለደቀ መዛሙርት ለመናገር ሮጡ። በመንገዳቸው ላይ የገጠማቸው ከሞት የተነሳው ጌታ ኢየሱስ እራሱ ነው። እነርሱም የእርሱን እግር ያዙ። እርሱ ስጋና ደም ያለው ኢየሱስ እራሱ እንጂ መንፈስ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሴቶቹ እርሱን መንካት ነበረባቸው። የትንሳኤውን ጌታ በህይወታቸው እንደተለማዱ ሰዎች ሁሉ እነርሱም በተመሳሳይ መልኩ ነው ምላሽን የሰጡት። እነርሱ አመለኩት! ኢየሱስ እነርሱ ከመልአኩ የሰሙትን ደግሞ ተናገራቸው፤ "አትፍሩ" አላቸው። ትዕዛዙም ተመሳሳይ ነው፤ "ሄዳችሁ …ለወንድሞቼ ተናገሩ…" በመልአኩ የተነገራቸውን ኢየሱስ አፀናላቸው፤ መቃብሩ ባዶ እንደሆነ ያዩትን አሁን ደግሞ በአይኖቻቸው ተመለከቱ በእጆቻቸውም ነኩት። ኢየሱስ ከሞት ተነስቷል፤ህያው ነው!

ምዕራፍ 4

**ትግበራ**

ነገር ግን ይህንን ታላቅ ክስተት ከሁለት ሺህ አመታት በፊት ከተደረገ ታሪክ በላይ እንዲሆን ያደረገው ምንድነው? ይህ ዛሬ ለእኔ ህይወት ምን አይነት ትርጉም አለው? እስቲ ቀጥለን የተወሰኑ ነገሮችን እንመልከት:

1. የኢየሱስ ትንሳኤ እርሱ ስለራሱ እና እኔ የጠፋሁና የተፈደብኝ ኃጢአተኛው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚኖረኝ ግንኙት የተናረውን ሁሉ የሚያረጋግጥ ነው። ከሁሉ በላይ የሆነውን እና አቻ የሌለውን የአባቱን ፍቅር ለእኛ ግልፅ አደረገው፤ይህንንም ያደረገው ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ በመስጠት ነው (ዮሐንስ 15:13)። ኢየሱስ የተናገራቸው በሙሉ ፍፁም እውነት ናቸው። ኢየሱስ የተናገራቸው ሁሉ ህይወት እና ድነትን ይሰጣሉ። በእርሱ የሚያምሙ ሁሉ የዘላለም ህይወትን ያገኛሉ። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርት በዮሐንስ 14:6 ላይ እንዲህ አላቸው "ኢየሱስም፦_____________መንገድና_____________ሕይወትም_____________፤ በእኔ በቀር ወደ _____________የሚመጣ የለም።"

   ሀ. ትንሳኤው እርሱ ለእኔ የተናገራቸውን ልክ እርሱ ስለራሱ የተናገረውን እንደሚያረጋግጥ ሁሉ ያረጋግጥልኛል?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

   ለ. ትንሳኤው ሁሉን ነገር የሚያረጋግጥ ከሆነ በእኔ እና በኢየሱስ መካከል ስላለው ግንኙነት ምን የሚሰጠኝ ትርጉም አለ?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

2. እግዚአብሔር የራሱን መለኮታዊ ሃይል በትንሳኤው ውስጥ አሳይቷል።

   ሀ. እርሱ ኢየሱስን ከሞት አስነሳው። የመሬት መንቀጥቀጥ የኢየሱስን ሰዎችን የማዳን ስራ ወይም መቤዠት እግዚአብሔር በመለኮታዊ ማህተሙ ያረጋገጠበት ነው። ይህ ማህተም ሲነበብ እንዲህ ይላል "ይቅር ተብሏል።" በእርግጥም ተፈፅሟል። ከአሁን በኋላ ከክርስቶስ ስራ ውጭ ለሰዎች ድነት የሚያስፈልግ ምንም ነገር የለም። ከአሁን በኋላ የኃጢአት ባሪያ አይደለሁም። ለእኔ ህይወት ኢየሱስ ላደረገው ነገር እግዚአብሔር የአደረገው የማረጋገጫ ማህተም ምንድነው? ይህ ምህረት ለእኔ የሚሰጠው ነገር ምድነው?

      i. ዮሐንስ 8:32፤ 36

      ________________________________________________________

      ii. ሮሜ 8:1፤ 2

      ________________________________________________________

iii. 2 ቆሮንቶስ 3:17

______________________________________________

iv. ገላትያ 5:1፤ 13

______________________________________________

ህይወቱ የኃጢአት ባሪያ በሆነና ህይወቱ ነፃ በሆነ ሰው መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው:

______________________________________________

______________________________________________

ለ. እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት ማስነሳት ብቻ ሳይሆን እኔን እና እናንተን ይህንን የትንሳኤ ሃይል እንድንለማመደው ይጋብዘናል። መልአኩ "ኑና እዩ..." አላቸው። መልአኩ ያሳያቸው ኢየሱስ ተቀብሮበት የነበረውን አሁን ግን ባዶ የሆነን መቃብር ነው። ኢየሱስ ለእኔ ሲል በእኔ ፈንታ ሞቶ ከሞት ባይነሳ ኖሮ የሚያሳየኝ የእኔን መቃብር ነበር። ሮሜ 6:6 እንዲህ ይላል፤ "ከእንግዲህስ ወዲያ ______________ እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ______________ ዘንድ አሮጌው ______________ከእርሱ ጋር እንደ ______________እናውቃለን፤ የሞተስ ______________ ጸድቋልና።" ቁጥር 8 ደግሞ እንደዚህ ይለናል፤ "ነገር ግን ______________ ጋር ______________ከእርሱ ጋር ደግሞ ______________ እንድንኖር እናምናለን።"

ሐ. የክርስቶስ ትንሳኤ የሚያረጋግጠው ኢየሱስ እንደተናገረው እግዚአብሔር የሕያዋን አምላክ መሆኑን ነው፤ "የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም (ማቴዎስ 22:32)።" ሌሎች የዓለም ሐይማኖቶች የሚያስተምሩት አምላካቸው ሁሉን ቻይ ነገር ግን ሊደረስበት የማይቻል ሐይል፤ "መለኮታዊ ሃይል፤" ወይም አምላክ ዝም ብሎ ፍልስፍና፤ያ ማለት ሙት አምላክ ማለት ነው። የክርስቶስ ትንሳኤ የሚያረጋግጥልን የእግዚአብሔርን የቅርብ አምላክ ፤ ከሰው ሁሉ ጋር የጠበቀ ህብረትን መመስረት የሚፈልግ አፍቃሪ አምላክ መሆኑን ሲሆን ይህ ማለት ደግሞ እግዚአብሔር ህያው አምላክ ። እግዚአብሔር አምላክ ለእኔ እና ለእናንተ በጣም የቀረበ እና የፍቅርን ህብረት ለእርሱ ጋር እንድንመሰርት ይጋብዘናል።

መ. ለዚህም ሌላ ተጨማሪ የምስራች አለ። እግዚአብሔር እኔን በኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ እንድሳተፍ በማድረግ ህያው አድርጎኛል። እርሱ በእኔ ስለሚኖር እና በእኔ ስለሚሰራ በሃይሉ ያቀጣጥለኛል። የመልአኩ ትዕዛዝ በቶሎ እንዲሄዱና እና እንዲናገሩ ነው። የኢየሱስ ትዕዛዝ እንዲሄዱ እና እንዲናገሩ ነው። ትዕዛዙ አልተለወጠም። ስለእርሱ ትንሳኤ ለሌሎች ሰዎች ሁሉ እንድናገር እኔም ታዝዣለሁ! የእርሱ ቃል እውነት ነው። እርሱ

እንደተናገረው እንዲሁ እንደቃሉ የሚሆን ጌታ ነው፡፡ እርሱ የተናገረው ነገር ሁሉ እውነት ነው፡፡ የእርሱን ትንሳኤ እንድናገር እና ለእኛ ያደረገውን ነገር ለሰዎች ሁሉ እንድናገር ወደዚህ ተልዕኮ ይጋብዘኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ዮሐንስ 10:10 የሚናገረን "_________________ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ _________________ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ" ይለናል፡፡

**ፀሎት**

እናንተ በኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ አማካኝነት የእግዚአብሔርን ፀጋ ስለተለማመዳችሁ፤ የእርሱን ትንሳኤ ለሰዎች ሁሉ እንድትናገሩ ስለተመረጣችሁ፤ በእርሱ ፀጋና ሃይል ህይወታችሁ ስለተቀጣጠለ፤የእርሱን ስራ በራሳችሁ ሐይል ብቻ እንድትሰሩ ስላልተዋችሁ ይልቁንም በመንፈሱ እንዳስታጠቃችሁ ስለምታውቁ ፀሎታችሁ የምስጋና እና የውዳሴ ነው፡፡____________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

_______________________________________________________________________________

# ትምህርት አራት

# አይኖቻቸው ተከፈቱ

## ማቴዎስ 28 እና ሉቃስ 24 — የትንሳኤው ቀን

---

**የትምህርት 4 ምልከታ**

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 4: ማቴዎስ 28:11-15፤ ሉቃስ 24:13-35

- ለውሸት የማባባያ ገንዘብ
- በአስቸኳይ ሂዱና ተናገሩ!
- በኤማሁስ መንገድ ላይ
- አስክሬኑን ፍለጋ
- ከህያው ጌታ ጋር የተደረገ ግንኙነት

## መግቢያ

ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እና እርሱን ሲያገለግሉ ለነበሩ ሴቶች ምን ዓይነት አስደናቂ ቀን ነው! እለቱ የጀመረው በማለዳ በመሬት መንቀጥቀጥ ሲሆን ያበቃው ደግሞ ከኢየሱስ ጋር የነበሩ ሰዎች ወደ ኤማሁስ ሲጓዙ ነው። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በጣም ብዙ ደስታ እና አይሁድን መፍራት ተቀላቅሎባቸው በተዘጋ ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል። አርብ እለት ሞተ ሰኞ ደግሞ ህያው ነው። አንዴ አስክሬኑ ጠፍቷል ወዲያወኑ ግን ኢየሱስ ህያው ጌታ ሆኖ ታያቸው። "ኑና እዩ" ተብለው የተነገራቸው አሁን ደግሞ "ሂዱና ተናገሩ" ተብሎ ታዝዘዋል። ይህ በእንዲህ እያለ የካህናት አለቆች እና የህዝቡ ሽማግሌዎች ስለመሬት መንቀጥቀጥ ፣ የድንጋዩ መንከባለል እና አስክሬኑ በዚያ አለመኖር የተናገሩትን ጠባቂ ወታደሮችን እያባበሉ ነው። እነዚህ ባለስልጣናት በቀረበው ሪፖርት ላይ ምን ሊያደርጉ ነው?

ቀኑን በሙሉ የተለያዩ አይኖች እየተከፈቱ ነው። የጠባቂዎቹ፤ የካህናት አለቆች እና ሽማግሌዎች፤ የሴቶቹ፤ የጴጥሮስ እና የዮሐንስ እና የሌሎች ደቀ መዛሙርት በሙሉ እና ተከታዮቹ በሙሉ ከዚህ በፊት ተለማምደው በማያውቁት መንገድ እውነት ተገልጦላቸው እየተመለከቱ ነው። እናተም ይህንን ጥናት እያጠናቸሁ ስትሄዱ የልቦናችሁ አይኖች ይከፈታሉ። የእግዚአብሔር መንፈስ ከሞት የተነሳውን ጌታ እና አዳኝ ይግለጥላችሁ።

## ትምህርት 4

<u>ምዕራፍ 1</u>

**መግቢያ**

ልክ እንደ ጵላጦስ፤ የካህናት አለቆች እና ሽማግሌዎች የኢየሱስን ጉዳይ ከአሁን በኋላ ማንሳት አልፈለጉም። ኢየሱስ ሙቷል፤ መቃብሩ ደግሞ ታትሞበት ታሽጓል። በምን መልኩ የኢየሱስ አስክሬን ከዚያ ማምለጥ አይችልም። ስለዚህ ጉዳይ ማቴዎስ የሚናገረንን እስቲ እንመልከት።

**የቤት ስራ**: ማቴዎስ 28:11-15 አንብቡት።

**መልመጃ**:

1. ሴቶቹ ወዴት ነው የሄዱት?

   ____________________________________________

2. ጠባቂዎቹ ወዴት ነው የሄዱት (ቁጥር 11)?

   ____________________________________________

3. ስለሆነው ነገር ምን ብለው ተናገሩ? ምን ሆነ?

   ____________________________________________

   ____________________________________________

4. ሁሉም ነገር በእቅዱ መሰረት እየሆነ አይደለም። አሁን የካህናት አለቆች እና ሽማግሌዎች መፍታት ያለባቸው ታላቅ ችግር አለ። እነርሱ ያወጡት እቅድ ምን ነበር (ቁጥር 12ለ-14)?

   ሀ. ለወታደሮቹ የሰጡት ነገር

   ____________________________________________

   ለ. ወታደሮቹ መናገር ያለባቸው

   ____________________________________________

   ሐ. ገዢው ነገሩን ከደረሰበት

   ____________________________________________

5. ቁጥር 15: "እነርሱም____________ ተቀብለው እንደ ____________ አደረጉ። ይህም ነገር ____________ ዘንድ እስከ ____________ ድረስ ____________ ይኖራል።"

**ማሰላሰል**:

1. በመጀመሪያ ይሁዳ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ገንዘብ ተሰጠው። አሁን ደግሞ በዚህን ሰዓት ገንዘብ የተሰጠው ጠባቂዎቹ እንዲዋሹ እና እንዲያታልሉ ነው። የካህናት አለቆች እና ፈሪሳውያን ኢየሱስ ስለእራሱ ትንሳኤ ያወራውን እንደማሳት ቆጥረው እርሱን አሳች ማለታቸው በጣም የሚገርም ነገር ነው (ማቴዎስ 27:63-64)። እውነት እንዳይነገር ዲያብሎስ የተጠቀመባቸው ሉሎች ሰዎች እነማን ናቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

2. አንዳንድ ሰዎች የወታደሮቹን እና የአለቆችን የውሸት ወሬ በመስማት እግዚአብሔር አንዲያ ልጁን ከሞት አላስነሳም ብለው ያምኑ አሉ። ለሰዎች የኢየሱስን አስክሬን የሆነ ሰው ሰርቆታል ብሎ መቀበል በጣም ቀላል ነው ነገር ግን ኢየሱስ ለሞት ተነስቷል ብሎ መቀበል ግን እምነትን ይጠይቃል። መፅሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 11:6 ላይ የሚያስተምረን "ያለ_______________ ደስ _______________ አይቻልም። እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ 1:17ለ እንዲህ ይላል፤ "የእግዚአብሔር_________________ከእምነት ወደ _________________ በእርሱ _________________።"

**ትግበራ**:

1. የአይሁድ እምነትን የሚመሩ ሰዎች የኢየሱስ አስክሬን አስመልክቶ የፈጠራ የውሸት ወሬን አሰራጩ። የእነርሱ ተግባር ሰዎች ማንን ማመን ይቻላል እንዲሉ የሚያደርግ ነው። እናንተ እውነትን ተናጋሪ ናችሁ? ሰዎች እውነት ተናጋሪ ናችሁ ብለው እናንተን በማመን ወደ እናንተ ይመጣሉ? ስህተታችሁን ዋሽታችሁ እንደማትደብቁ ሰዎች ያምኗችኋል? ወይም እውነትን መናገር ይከብዳችኋል።
2. እውነት ከሆነው ከእርሱ ጋር ያላችሁን ግንኙነት እንዴት ትገልፁታላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

3. የሃይማኖት መሪዎች የውሸታቸው እስረኞች ሁነዋል። ወታደሮቹ አንድ ቀን የተመለከቱትን እውነት ይገልጡ ይሆን? ተጨማሪ ገንዘብ ይፈልጉ ይሆን? እነርሱ የኖሩት ገዢው (ጵላጦስ) እውነቱን ያውቅ ይሆናል በማለት በፍርሃት ውስጥ ነው። ጵላጦስን ሊያሳምነው ይቻላል ብለው ያሰቡት ነገር ምን ሊሆን ይችላል? የእነርሱ ውሸት እና የማሳት ተግባር ተጨማሪ ወሸቶችን እና የማሳሳት ተግባሮችን ይፈልጋል። እግዚአብሔር የሚፈልገው ይህንን አይደለም። መልአኩ የተናገረው "በፍጥነት ሂዱና የእርሱ ደቀ መዛሙርት ንገሯቸው" ብሎ ነው። እውነቱ ይነገር። እርሱ ተነስቷል! ምናልባት ወታደሮቹ እንደሞተ ሰው ከተኙበት የመነሳት እድልን ሳያገኙ

ሴቶች ከመቃብሩ ስፍራ ፈጥነው እየሄዱ ነው። እነርሱ ፈርተዋል ደግሞም በደስታ ተሞልተዋል። እነርሱ ይናገራሉ! ኢየሱስ በመንገድ ላይ አግኝቷቸው ፍርሃታቸውን አስወግዷል፤እርሱም "አትፍሩ፤ሂዱና ተናገሩ!" አላቸው። ሴቶቹ ለደቀ መዛሙርት ሄደው ለመናገር የነበራቸው መበረታታት ለእኛም የኢየሱስን ትንሳኤ እውነት ለሰዎች እንድንናገር ጉልበትን ይሰጠናል። ታሪኩን ከሴቶቹ ሰምታችኋል። በዚያን እለት ማለዳ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። የጌታን ትንሳኤ ለሌሎች ሰዎች ለመናገር እየሮጣችሁ ነው፤ በደስታ ተሞልታችኋል? ለማን ነው መናገር የምትፈልጉት? ኢየሱስ ህያው ጌታ እንደሆነ ማነው ማወቅ ያለበት?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ፀሎት**

ጌታ ሆይ አንተ የእኔ ህያው ጌታ ነህ። አንተ ከሞት ተነስተሃል። መልአኩ፤ "እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም" ብሎ ተናገራቸው። የከፈኑ ጨርቅ እዚያው ቀርቷል። ከአሁን በኋላ በፍርሃት ውስጥ መኖር የለብኝም፤ ስለጌታ ትንሳኤ ለሰዎች እንድናገር ከፍርሃቴ። ማንም ሰው በሞት ፍርሃት ውስጥ እንዳይኖር ስለትንሳኤ እውነቱን ለመናገር እንድችል ድፍረቱን ስጠኝ። አንተ ከሞት እንደተነሳህ ሁሉ በአንተ ያመኑ ሁሉ በትንሳኤ ከሞት ይነሳሉ። የተቤዠኝን ጌታ ህያው መሆኑን ማወቁ እንዴት ደስ የሚል እና የሚያፅናና ነገር ነው።

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ምዕራፍ 2**

**መግቢያ**:

ይህ የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ከሌሎች የሳምንቱ ቀናት ይልቅ የተለየ እና ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ እንደዚያ አይነት ቀን አልነበረም ደግሞም አይኖርም ብሎ ማሰቡ አላስፈላጊ ነው። የሰው ስሜት አይሎ ወደ ሁከትና ሽብር ተለውጧል። በመጀመሪያ፤ ኢየሱስ መሞቱን ማወቃቸው ሴቶቹን ወደ መቃብሩ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል (ማርቆስ 16:1)። አስክሬኑ በመቃብሩ ውስጥ የለም የሚለው ዜና ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ወደ መቃብሩ እንዲሮጡ አድርጓቸዋል (ዮሐንስ 20:3-8)። የኢየሱስ ለሴቶቹ መገለጡ ለደቀ መዛሙርቱ ስለሰሙት እና ስላዩት ነገር ለመናገር በራስ መተማመናቸውን ጨምሯል (ማቴዎስ 28:10) ። ኢየሱስ ለመግደላዊት ማርያም ከሞት የተነሳ ጌታ እንደሆነ መገለጡ ለእርሷ የአዲስ ህይወት ደስታን እና መፅናናትን ሰጥቷታል (ዮሐንስ 20:10-18)።

ጴጥሮስ በሆነው ነገር እየተደነቀ ነው (ሉቃስ 24:12)። ነገሮች ሁሉ በፍጥነት እየሆኑ ያለ ይመስላል። ጴጥሮስ በየጊዜው የተለያዩ ሰዎችን ሲያገኛቸው ስለሆነው ነገር ከእነርሱ ተጨማሪ ዜናን ለመስማት ወደ እነርሱ ይቀርባል። በመንገድ ላይ እየተጓዙ ስለሚገኙ ስለሁለቱ ደቀ መዛሙርት ታሪክ ቀጥለን እንመልከት…

**የቤት ስራ**: ሉቃስ 24:13-35 አንብቡት።

**መልመጃ**:

1. እለቱ ምን ነበር (ቁጥር 1)?

   ______________________________________________

2. ሁለቱ ሰዎች ወዴት እየሄዱ ነው (ቁጥር 13)?

   ______________________________________________

3. ስለ ምን እያወሩ ነበር (ቁጥር 14)?

   ______________________________________________

4. እነርሱ እየሄዱና እና እየተነጋገሩ እያሉ ምን ሆነ (ቁጥር 15)?

   ______________________________________________

5. በዚያ ስፍራ የሆነው አስደናቂ ነገር ምንድነው (ቁጥር 16)?

   ______________________________________________

6. ከጉዟቸው ቆም እንዲሉ ያደረጋቸው የኢየሱስ ጥያቄ ምንድነው (ቁጥር 17)?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

7. ፊታቸው ምንን ያንፀባርቅ ነበር (ቁጥር 17)?

   ______________________________

8. ቀለዮጳ ኢየሱስን ምንድነው የጠየቀው (ቁጥር 18)?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

9. ኢየሱስ ምን ብሎ መለሰላቸው (ቁጥር 19ሀ):

   ______________________________________________

10. በቁጥር 19 ላይ የናዝሬቱ ኢየሱስን እንዴት የገለፁት?

    ሀ.____________________________________________

    ለ.____________________________________________

11. እነዚህ ሰዎች የትኛውን ድርጊት ነው ከኢየሱስ ጋር ያገናኙት(ቁጥር 20-24)?

ሀ.ቁጥር 20:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ለ.ቁጥር 21: የእነርሱ ተስፋ ምን ነበር?

___________________________________________________________

ሐ.ይህ ከሆነ ምን ያህል ጊዜ ሆነው?

__________________________________________________________

መ. ቁጥር 22 እና 23: ሴቶቹ ምን አደረጉ?

i. ________________________________________________________

ii. ________________________________________________________

ሠ. ቁጥር 24: ከእነርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች ምን አገኙ?

_________________________________________________________________

_________________________________________________________________

12. የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 25)?

___________________________________________________________________

እና

___________________________________________________________________

13. ኢየሱስ ምንድነው የጠየቃቸው (ቁጥር 26)?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

14. ኢየሱስ ሙሴን እና ነቢያትን የተጠቀመው ለምንድነው (ቁጥር 27)?

___________________________________________________________________

15. ወደ መንደር ሲቀርቡ ምን ሆነ (ቁጥር 28-29)?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

16. በማዕድ ላይ ተቀምጠው እያለ ኢየሱስ ምን አደረገ (ቁጥር 30)?

___________________________________________________________________

___________________________________________________________________

17. በሁለቱ ሰዎች ላይ ምን ተከሰተ (ቁጥር 31)

___________________________________________________________________

18. በኢየሱስ ላይስ ምን ሆነ?

_______________________________________________

19. እርስ በእርሳቸው ምን ተባብለው ተጠያየቁ (ቁጥር 32)?

_______________________________________________

_______________________________________________

20. እነርሱ የሚነግሩት ታሪክ አላቸው! እነርሱ ምን አደረጉ (ቁጥር 33)?

_______________________________________________

21. እነማን ናቸው የተሰባሰቡት?

_______________________________________________

22. የተሰባሰቡ ሰዎች ምን አሉ (ቁጥር 34)?

_______________________________________________

23. ወደ ኤማሁስ የተጓዙት ሰዎች ምነድነው ለሌሎች የተረኩት ነገር (ቁጥር 35)?

ሀ.______________________________________________

ለ.______________________________________________

<u>**ምዕራፍ 3**</u>

**ማሰላሰል**:

1. ከጥቂት ቀናት በፊት ስለሆነው ነገር እየተነጋገሩ ወደ ኤማውስ ይጓዙ የነበሩትን ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ መገመት ይቻላል፡፡ ለእነርሱ ትልቁ ነገር የጌታቸው መከራ እና ሞት ነው፡፡ አሁን ለእነርሱ ነገሮችን ያወሳሰበው ነገር መቃብሩ ባዶ መሆኑና የአስክሬኑ አለመኖርን ወሬ መስማታቸው ነው፡፡ ሴቶቹ ጌታቸውን በመቃብሩ ውስጥ የለም፡፡ ጴጥሮስ እና ዮሐንስ ሴቶቹ የተናገሩትን ወሬ ለማረጋገጥ ወደ መቃብር ሄዱ ነገር ግን የእርሱን አስክሬን አላገኙም፡፡ የኢየሱስ መከራ እና ሞት ይሆን እንዴ የእርሱን አስክሬን እንዲጠፋ ያደረገው? ሁሉም ሰው የሚነጋገረው ስለዚህ ይሆን እንዴ? መልአኩ ምንድነው የተናገራቸው (ሉቃስ 24:5ለ-6)?

   _______________________________________________

   የእናንተ ሐሳቦች:

   _______________________________________________

   _______________________________________________

2. ከእነዚህ ሰዎች ጋር በዚያ መንገድ ላይ የምትጓዙ ብትሆኑ ምን አይነት ነገር ነው ከእነርሱ ጋር የምትነጋገሩት?

   _______________________________________________

**ትግበራ**:

1. በህይወቴ የሚከሰቱ ነገሮች እና ሁኔታዎች ኢየሱስን እንድመለከት የሚያደርጉ ናቸው? በእናንተ ህይወት ውስጥ የተከሰቱ ነገሮች ወይንም ሁኔታዎች ኢየሱስን ግልፅ ያልሆነና ልትረዱት የማትችሉት አይነት ሰው እንደሆነ እንድታስቡ አድርጓችሁ ያውቃል:

   ______________________________________________

   ______________________________________________

2. ስለ ኢየሱስ ያለኝ የእኔ ግምት ምንድነው? ለእኔ ፤ ለቤተሰቦቼ እና ለወዳጆቼ ምን እንዲያደርግ ነው ከእርሱ የምጠብቀው?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   እርሱን ለሚከተሉ ሰዎች ምን እንዲያደርግላቸው ነው እኔ የምጠብቀው?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

   ኢየሱስ ለእኔ ለግሌ እንዲያደርግልኝ የምጠብቀው ነገር እንዴት አድርጎ ነው የኢየሱስን ማንነት እንዳላይ የሚያደርገኝ?

   ______________________________________________

   ______________________________________________

3. ሰዎቹ የኢየሱስን አስክሬን በመቃብሩ ውስጥ እንደሚያገኙት ጠብቀው ነበር፡፡ እኔ ኢየሱስ የት ነው የምፈልገው? የት እንደማገኘው ነው ተስፋ የማደርገው?-

   ______________________________________________

4. ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስን የት እንደሚያገኙት ነው የተናገረው (ሉቃስ 24:27)

   ______________________________________________

   ______________________________________________

<u>**ምዕራፍ 4**</u>

**ማሰላሰል**:

1. ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ኤማሁስ ሲደርሱ ቀኑ ስለመሸ ኢየሱስን እራት ከእነርሱ ጋር እንዲበላ ጋበዙት፡፡ ቁጥር 29 ላይ እነርሱ "ግድ አሉት" ይላል፡፡ ለእንግዳ መስተንግዶን ማድረግ ትልቅ በረከት፡፡

   ሀ. ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ ቃላት ያበረታታናል፤

   "______________________________________________

   ______________________________________________ (ሮሜ 12:13)፡፡"

ለ.በዕብራውያን 13:2 ላይ: "በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ ________________ እንግድነት ________________::"

2. ኢየሱስ አሁን ለእነዚህ ሰዎች ራሱን ሊገልጥ ነው፡፡ እርሱ ከእነርሱ ጋር በማዕድ ተቀምጦ እያለ፤
   ሀ. እንጀራውን ______________________________________________፤
   ለ. ቆርሶም________________________________________________፤
   ሐ. ______________________ ተከፈተ፡፡
3. ቀኑን በሙሉ ትልቅ ነገር የሆነ ቢሆንም ኢየሱስ ግን እነርሱ እንዲያውቁት የፈለገው አንድ ነገር አለ፡፡ ለእራት በማዕድ በተቀመጡ ጊዜ ምንድነው የሆነው (ቁጥር 31)? "__________________ ተከፈተ፥ __________________፤ እርሱም ከእነርሱ __________________:: " እነርሱ ህያው ከሆነው ጌታ ኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ዋሉ፤ አመሹ፤በመጨረሻም ለእራት ጋበዙት፤ አይናቸውም ተከፈተ!

**ትግበራ ጥያቄS**:

1. እርሱ ከእኔ ጋር እየሄደ ቅዱሳን መፃህፍትን እየጠቀሰ ሲናገረኝ ልቤ በውስጤ ይቃጠል ነበር፤ ይህ ምን ዓይነት የሚያስደንቅ ልምምድ ነው?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

2. ይህ የ "ልብ መቃጠል" ልምምድ በእኔ ህይወት ላይ የሚያመጣው ምን ዓይነት ለውጥ ይኖራል?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

**ፀሎት**

ቅዱስ ጌታ ሆይ፤ ትንሳኤ ሙሉ በሙሉ ስለአንተ የሚናገር ነው፡፡ አንተ እስራኤልን እንድትቤዥት ከአባት ዘንድ የተላክ ነህ ፡፡ አንተ እኔን እንድትቤዠት ከአባት ዘንድ የተላክ ነህ ፡፡ የአንተ ቃል የእኔን ዓይኖች ከፍተው አንተን እንድመለከት እና ልቤ እንዲቃጠል አድርጓል፡፡ አንተ ከሞት እንደተነሳህ ይህንን እውነት ለሌሎች መናገር እንድችል ሃይልን እና የጋለ ፍላጎትን ስጠኝ! ለአንተ ምስጋናን እና ውዳሴን ሳላቋርጥ አቀርባለሁኝ፡፡

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ትምህርት አምስት

# እልካችኋለሁ

## ዮሐንስ 20:19-23 — ኢየሱስ፤ የእኔ ሰላም

---

**የትምህርት 5 ምልከታ**

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 5:  ዮሐንስ 20:19-23

- አይሁድን ፈርተው
- ኢየሱስ ተገለጠ
- የእርሱ ሰላም ስጦታ
- የእርሱ እቅድ ስጦታ
- የእርሱ ሃይል ስጦታ
- የእርሱ ዓላማ ስጦታ

## መግቢያ

በዚያን እለት የነበረው እንቅስቃሴ ሁሉ ያበቃው በዚያ ስፍራ የተሰባሱት የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት በአካላቸው እና በስነ ልቦናቸው በጣም ተዳክመው ነው ብሎ ማሰብ ይቻል ይሆናል፡፡ ነገር ግን ለደቀ መዛሙርቱ እለቱ አላበቃም፡፡ ወደ ኤማሁስ ይጓዙ የነበሩት ደቀ መዛሙርት ረጅሙን እና አድካሚውን እለቱ ያጠናቀቁት በእለቱ የገጠማቸውን ለሌሎች ለማካፈል በጉጉት ወደኋላ በመመለስ ነው፡፡ ኢየሱስ ዳግም በተገለጠላቸው ጊዜ እነዚህ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት የገጠማቸውን ነገር ለሌሎች እየተረኩላቸው ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ ይህ የሆነው የት ነው?

ከሞት የተነሳው ጌታ ለተከታዮቹ ስጦታን ሰጠ፡፡ ትምህርት አምስትን ስታጠኑ እነዚህን ስጦታዎችን ልብ በሏቸው! እነዚህ ስጦታዎች ለመጀመሪያዎቹ የጌታ ደቀ መዛሙርት የተሰጡ ሲሆን ለእኛ ደግሞ የተላለፉልን ናቸው፡፡ ጌታ የሰጠንን እነዚህን ስጦታዎችን በምስጋና ተቀበሏቸው፡፡ ኢየሱስ ስለእነዚህ ስጦታዎች ሲናገር በጥንቃቄ አድምጡት እና እወቋቸው፡፡ በእነዚህ ስጦታዎች እንዴት አድርጋችሁ በሰማይ ያለውን ቅዱስ አባቱን እና የእርሱን ስም ማክበር እንደምትችሉ ኢየሱስን ጠይቁት፡፡

## ትምህርት 5

<u>ምዕራፍ 1</u>

**መግቢያ**

የሚቀጥለው ታሪክ ተመዝግቦ የሚገኘው በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ነው። ወደ ኤማሁስ ይጓዙ የነበሩ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ከተገለጠላቸው በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም እንደተመለሱ ተነግሮናል (ሉቃስ 24:33)። እነርሱ ኢየሩሳሌም በደረሱ ጊዜ አስራ አንዱ ምንድነው የነገሯቸው (ቁጥር 34)?

1. ______________________________________________________________
2. ______________________________________________________________

ከዚያ በኋላ ሁለቱ ደግሞ የነገሯቸው ነገር (ቁጥር 35):

1. ______________________________________________________________
2. ______________________________________________________________

ሉቃስ በቁጥር 36 ላይ የሚነግረን ነገር "ይህንም______________________ኢየሱስ ራሱ______________________ቆሞ። ______________________ ለእናንተ ይሁን አላቸው።!'" ይህንን ታሪክ ዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ውስጥ ቀጥለን እንመለከታለን።

**የቤት ስራ**: ዮሐንስ 20:19-23 አንብቡት።

**መልመጃ**:

1. ሰዓቱ ስንት ነበር (ቁጥር 19)?

   ______________________________________________________________

   ሀ. በዚያን እለት ጠዋት በማለዳ ምን ሆነ (ቁጥር 1 - )?

   ______________________________________________________________

   ለ. ምንድነው የተፈጠረው ግራ መጋባት (ቁጥር 2፧ 9)?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

2. ደቀ መዛሙርቱ የት ነበሩ? አካባቢው ምን ይመስል ነበር (ቁጥር 19)?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

3. ለምንድነው እነርሱ የፈሩት?

   ______________________________________________________________

4. ዮሐንስ የሚነግረን ነገር “ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ _______________ በመሸ ጊዜ፥ _______________ ተሰብስበው በነበሩበት፥ _______________ ስለ ፈሩ _______________ ተዘግተው ሳሉ፥ _______________ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆመ።” (ቁጥር 19)።
5. የእርሱ ሰላምታ ምን ነበር?

   ___________________________________________

6. ሉቃስ 24:37 የሚነግረን የደቀ መዛሙርቱ ምላሽ ምን ነበር:

   ___________________________________________

7. ኢየሱስ እነርሱን ስለ ምን _______________? ስለ ምንስ _______________ ይነሣል? በማለት ጠየቃቸው። ኢየሱስን ሲመለከቱ የመሰላቸው ነገር ኢየሱስ _________ እንደሆነ ነው።
8. ደቀ መዛሙርቱ እርሱን ሲመለከቱ ከገቡበት ፍርሃት ለማውጣት ኢየሱስ ምንድነው የነገራቸው (ሉቃስ 24:39)?

   ሀ. ___________________________________________

   ለ. ___________________________________________

9. የእርሱ እጆች እና እግሮች ሲመለከቱ ያደረጉት ነገር ምንድነው (ቁጥር 41)?

   ___________________________________________

   ___________________________________________

10. የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 20 በድጋሚ ተመልከቱ። ዮሐንስ የሚዘግበው፤ “ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ _______________” (ቁጥር 20ለ) በማለት ነው።

**ማሰላሰል**:

1. በተዘጋ ቤት ውስጥ የነበሩት ሰዎች ተዳክመው እንደነበር መገመት አያስቸግርም። ቀኑ በጣም ረጅም ነበር፤ እለቱ የጀመረው በማለዳ ሴቶቹ የተናገሩት ነገር፤ ይህንን ለማረጋገጥ ዮሐንስ እና ጴጥሮስ ወደ መቃብር ያደረጉት እሩጫ፤ በትንሳኤው ዮሐንስ ሲያምን ጴጥሮስ ግን በሆነው ነገር ግራ ተጋብቷል። በዚህ ሁሉ ግራ መጋባት መካከል ነው መግደላዊት ማርያም ጌታን እንደተመለከተች ተናግራ እያለች ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ከኤማሁስ ተመልሰው በዚያ ኢየሱስ እንደታያቸው ተናገሩ። በዚያን ቀን የሆነ ሌላ ተጨማሪ ነገር ምን አለ? እራሳችሁን በእነርሱ ቦታ አስቀምጡ። በዚህ ሁሉ መካከል ምንድነው የምታደርጉት?

   ___________________________________________

   ___________________________________________

2. በዚያን ጊዜ በዚያን ስፍራ የተደበላለቀ ስሜቶች ነበሩ። ያለጥርጥር በፍርሃት ውስጥ ነበሩ ወዲያውኑ ተስፋቸው ህያው ሆነ። ተጨንቀውና ፈርተው ነበር ከዚያ በኋላ በጣም ደስ አላቸው በሆነውም ነገር እጅግ ተደንቀዋል...የማይቻል የሚመስል ነገር እውነት ሆነ። ሁሉ በላይ እንዴት ከሞት ሊነሳ ቻለ? እነርሱ የሚያውቁት የእርሱን መሞት ነው። ኒቆዲሞስ እና ዮሴፍ ቀብረውታል። አሁን ደግሞ እርሱ በሁሉም ስፍራ እየታየ ነው። ይህንን ጉዳይ ምን ታደርጉታላችሁ?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

***<u>ምዕራፍ 2</u>***

***መልመጃ***:

1. ኢየሱስ ቀደም ብሎ የተናገረውን ደገመው: "_____________________________________
   (ዮሐንስ 20:21ሀ)።"
2. ከዚያም እርሱ ለእነርሱ "____________________እንደ ላከኝ ____________________ደግሞ ____________________ አላቸው።"
3. ቁጥር 22: ከዚያ ምን አደረገ?

   ________________________________________________________________________

   ከዚያ በኋላ ምን ሆነ?

   ________________________________________________________________________
4. ቁጥር 23: ቀጥሎ ምን ተናገራቸው?

   ________________________________________________________________________

   ________________________________________________________________________

## ትምህርት

ኢየሱስ፤ የትንሳኤው ጌታ፤ ለራሱ ህዝብ ስጦታን ሰጣቸው፤ ይህ ስጦታ ዛሬም የእርሱን ጥሪ ሰምተው ለሚሰማሩ ሁሉ ነው፤ማለትም ለእኔና ለእናንተ። እነዚህ ስጦታዎች በዮሐንስ 20:21-23 ውስጥ ተጠቅሰዋል።

1. ኢየሱስ የሰጣቸው ስጦታ የእርሱን *ሰላም ነው*።
   እነዚህ ሰዎች ከሰላም የበለጠ ምን ዓይነት ይፈልጉ ይሆን? እነርሱ ከሰላም ውጭ ሁሉን ነገር ተለማምደውታል። መሪያቸው ተገድሏል። አንዱ ጓደኛቸው አለቃቸውን አሳልፎ ሰጥቷል እንዲሁም እራሱን ገድሏል። ከእነርሱ የሐይማኖት መሪዎች የዚህን ዓይነት አመፅን እና ጥላቻን አይተው አያውቁም። እስራኤል ከሮማውያን ጭቆና ነፃ የምትወጣበት ህልማቸው

አሁን ተኮላሽቷል። የጠበቁት ነገር ሁሉ ድምጥማጡ ጠፍቷል። እነርሱ ሁሉም የጠበቁት መሪያቸው ከመስቀል ላይ ወርዶ ራሱን ሲያድን ሲሆን ነገር ግን እርሱ ሞቶ ለህይወታቸው እንዲፈሩ አድርጓል።

ከተዘጉ በሮች በስተጀርባ ምን እየተካሄ ይሆን? ስለሆኑት ነገሮች እየተነጋገሩ፤ እንዴት ነገሮች በፍጥነት እንደሆኑ እና እንዴት አድርጎ እርሱ እንዳስጠነቀቃቸው እየተወያዩ ነው? እርሱ የተናገራቸውን እያስታወሱ ይሆንን? እርሱ የተናገራቸውን ነገሮች በሙሉ ይሆናል ብለው ሳያምኑ ቀርተው እንደነበር አምነው ይሆንን? የሞታል ብለው ብለው እንዳላመኑ አሁን መሞቱን ሲመለከቱ ምን ይሉ ይሆን? እርሱ እንደተናገራቸው ኢየሱስ ለብቻው ትተውት ሲሸሹ የተሰማቸው ስሜት እንዴት ነበር? አሁን አይሁድን በመፍራት ተውጠዋል። መች ይሆን አይሁድ እነርሱን ተከትለው እስካሉበት ድረስ የሚመጡት? እነርሱ የእርሱ ተከታይ እንደነበሩ ሁሉም ሰው ያውቃል።

የራሳቸውን ሃይል ማጣት ማለት ምን እንደሆነ በትክክል ተለማምደውት ይሆንን? በመሪያቸው ላይ ምንም ሃይል አልነበራቸውም። በዚህን ጊዜ እርሱ የት እንዳለ የሚያውቁት ነገር የለም። በሁኔታዎች እና በሞት ላይ ጉልበት የላቸውም። በፍርሃታቸው እና በወደፊቱ ህይወታቸው ላይ ጉልበት የላቸውም። እነርሱ አቅመቢስ ሆነዋል! በእነዚህ የተስፋ መቁረጦች፤ ፍሃቶች እና በነገሮች ላይ እርግጠኛ መሆን በአልተቻለበት ጊዜ ውስጥ ጌታ ሰላም ለእናንተ ይሁን አለ! ሰላምን ስጦታ አድርጎ ሰጣው። በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳቦች:

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

__________________________________________________________________

ሰላም የእኛ ነው። ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት ይፈውሳል ከሰዎች ጋርም ያለንን ግንኙነት ያድሳል። ሰላም እኛን በመስቀል ላይ ከፈሰሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከእግዚአብሔር አብ ጋር ያስታርቀናል። ሰላም እርሱ የዓለም አዳኝ ነው ብሎ ለሚያምን ሁሉ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። ሰላም የእግዚአብሔርን እቅድ እንድንሰማ እና የእርሱን ግብዣ ሰምተን እንዲሁም የእርሱን ፈቃድ እና የእርሱን ፍቅር አውቀን ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ እርሱ ለሚያቀርበው ግብዣ ተሳታፊዎች እና ታዛዦች እንድንሆን ያደርገናል። ሰላም የመንፈሱን ሃይል እንድንቀበል፤ የእርሱን ምህረት እና ይቅርታ እንድናምን እና እንድንኖርበት ያደርገናል። ሰላም ተስፋን እና አዲስ ህይወትን ከትንሳኤው ጌታ ኢየሱስ እንድንቀበል ያስችለናል። በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳቦች:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ትግበራ**:

1. ፍርሃታችሁ ምንድነው? "ሰላም ለእናንተ ይሁን" የኢየሱስ ሰላምታ ሃሳብ ያረጋጋችኋል? እርሱ ወደ እናንተ ይመጣል። እርሱ ራሱ እንደሆነ በመገኘቱ (እርሱን በመዳሰስ፤እርሱን በማቀፍ እና እርሱ ራሱ እንደሆነ በማየት) ታውቁታላችሁ። እርሱ ህያው ነው! እርሱ ሞትን አሸንፏል!

- ኢየሱስ ህያው ነው! በህይወታችሁ ውስጥ በተቆለፈ ነገራችሁ ውስጥ፤ በልባችሁ ውስጥ መምጣት ይፈልጋል። እናንተ የተደበቃችሁበትን ማንኛውንም ዓይነት ግድግዳ፤ በሮች፤ ቁልፎች እና መከላከያዎችን አልፎ ወደ እናንተ መምጣት ይፈልጋል። እናንተን "ሰላም ለእናንተ ይሁን" ማለት ይፈልጋል። እርሱ ራሱን ሊሰጣችሁ ይፈልጋል።

2. በየትኛው ህይወታችሁ ላይ ነው እርሱ የሰላም ስጦታውን እንዲሰጣችሁ የምትፈልጉት?

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**<u>ምዕራፍ 3</u>**

**ትምህርት** (የቀጠል):

2. ኢየሱስ የራሱን የስጦታ እቅድ ይሰጣል።

   እርሱ ለእነርሱ እንዲህ አላቸው፤ "አብ እንደላከኝ ፤ እኔም እልካችኋለሁ።" ይህ ስጦታ ነው እንዴ ብለን ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን። እግዚአብሔር አብ ላከው እርሱም ተሰቀለ። አሁን እርሱ እኔን እየላከኝ ነው? ስለዚህ አላውቅም...

   እርሱ እቅድ አለው፤ እርሱ ለዓለም ባለው ራዕይ ውስጥ እኔም እንድሳተፍ ይጋብዘኛል። እርሱ ለዓለም ያለው ራዕይ ከጥንት ጀምሮ በስራ ላይ ነው። የእርሱ እቅድ የራሱን መንግስት ማቋቋም ሲሆን የሰው ልጆች ሁሉ በመንግስቱ ውስጥ እንዲሳተፉ ይፈልጋል። የትንሳኤው ጌታ በዚያ ለተሰበሰቡት ሰዎች የሚነግራቸው እነርሱ የእቅዱ አካል እንደሆኑና እቅዱም ቀላል እንደሆነ ነው:

   ሀ. እልካችኋለሁ። እኔ ስልጣን አለኝ። ስልጣን ተሰጥቶኛል። እኔ ስለምላካችሁ እናንተ የምትሄዱት እና የምትንቀሳቀሱት በእኔ ስልጣን ነው።

   ለ. እናንተ የእኔ ምስክሮች ትሆናላችሁ። ስለራሳችሁ ሳይሆን ስለእኔ ትመሰክራላችሁ። የተመለከታችሁትን፤የሰማችሁትን እና የምታውቁትን ትመሰክራላችሁ።

መ. እስከ አለም መጨረሻ ድረስ ትሄዳላችሁ፡፡ ይህ የእኔ ራዕይ ነው፡፡

**ትግበራ**:

1. የኢየሱስ ስጦታ የሆነው የእርሱ እቅድ ያስፈራችኋል? የሆነ ሰውን ስልጣን ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ? እርሱ በስልጣኑ ስልጣንን ሰጥቷችሁ በስራው እንድትሳተፉ ያደረገው እቅዱ ለህይወታችሁ ምን ዓይነት ትርጉምን ይሰጣችኋል: ________________________________

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

2. በእርሱ እንደተላክን መረዳት እና "ሂዱ" ወደ አለን ስፍራ መሄድ የእርሱን ሰላም እ ሃይል ይሰጣል?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

3. ኢየሱስ ለራሴ እንድሞት እየጠየቀኝ ነው፡፡ እርሱ የሞተው እኔ በህይወት እንድኖር ነው፡፡ የእኔ መሞት ያስፈለገበት ምክንያት በእኔ ለራሴ ፍላጎት መሞት እና በእኔ ህይወት ሰዎች ወደ ጌታ በመምጣት ዘላለማዊ ህይወትን ከእርሱ ያገኙ ይሆንን?

   ________________________________________________________________

   ________________________________________________________________

**ፀሎት**

ትንሽ ጊዜ ውሰዱ፤ እርሱ ስለሰጣችሁ የሰላም ስጦታ እና በስልጣኑ እናንተን በእቅዱ መሰረት ስለተላካችሁ አመስግኑት፡፡

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ትምህርት** (የቀጠል):

3. ኢየሱስ የእርሱ *ሃይል* ስጦታን ይሰጣል ፡፡

   "ይህንም ብሎ ________________አለባቸውና፡፡

   ____________________ተቀበሉ፡፡______________________ ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ ______________________ ተይዞባቸዋል አላቸው፡፡ (ዮሐንስ 20:22)፡፡" እርሱ እፍ አለባቸው፡፡ የእርሱ እስትንፋስ ህይወት አለው ህይወትን ይሰጣል፡፡ በዘፍጥረት 2 እግዚአብሔር ሰውን ፈጠረ፡፡ ቁጥር 7ለ የሚናገረን ምንድነው?

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

በኢሳያስ 42:5 ላይ እንዲህ ይላል፤ "ሰማያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፥ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያጸና፥ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ ሕዝብ __________________ ፥ ለሚሄዱባትም __________________ የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር።"

የእግዚአብሔር ሃይል የእርሱ ስጦታ ሆኖ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ወደ እኛ ይመጣል ። ሉቃስ 24:49 እንዲህ ይላል፤ "እነሆም፥______________________ የሰጠውን ተስፋ እኔ ______________________።" በዮሐንስ 20:22 "መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ" ይላል። እርሱ ወደ ውስጥ በደንብ ተንፍሱ፤የእኔ መንፈስ ወደ ውስጥ አስገቡ ያላቸው ይመስላል። The መንፈስ ቅዱስ የእርሱን እቅድ የምፈፅምበትን ሃይል ይሰጠናል! በእርሱ መንፈስ የማንሻገረው ተራራ፤ የማናልፈው መሰናክል የለም። ምክንያቱም እግዚአብሔር እራሱ ነው ከእኛ ጋር የሚሰራው። እኛ በራሳችን ምንም ማድረግ የምንችለው ነገር የለም ነገር ግን በእግዚአብሔር ሃይል ተልዕኮአችንን መወጣት እንችላለን። እኛ እርሱን በራሱ ተልዕኮ ላይ ተቀላቅለነዋል።

**ትግበራ**:

1. በየእለቱ የእግዚአብሔር መንፈስ የእኔን ህይወት እንዲያነቃቃ እጠይቀዋለሁ፤ በዚህም እኔ…
   ሀ.____________________________________________________________
   ለ.____________________________________________________________
2. በእየለቱ ጌታን የምጠይቀው ነገር ወደ እግዚአብሔር እቅድ ውስጥ ገብቼ በእርሱ ስራ ውስጥ እንዳልሳተፍ እና ወንጌልን እንዳልሰብክ ከሚያደርጉኝ ነገሮች ነፃ እንዲያወጣኝ እጠይቀዋለሁ፤ እነርሱም…
   ሀ.____________________________________________________________
   ለ.____________________________________________________________

**ፀሎት**

በየእለቱ በእርሱ ስራ ላይ እንድሳተፍ ስላደረገኝ አመሰግነዋለሁ:

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 4

**ትምህርት** (የቀጠል):

4. ኢየሱስ የሚሰጠን ሌላው ስጦታ የእርሱ ***ዓላማ ነው***።

   የኢየሱስ ዓላማ ፤ የእርሱን መንፈስ የሰጠበት ምክንያት በእኛ ህይወት እና አገልግሎት ሌሎች ሰዎች የኃጢአት ይቅርታን እንዲያገኙ ነው። ይቅርታ ለኃጢአተኛ የሚሰጥ ስጦታ ነው። ኢየሱስ ኃጢአታችንን በላዩ ላይ አድርጎ እኛን ይቅር አለን ። የእግዚአብሔር ፍቅር የእግዚአብሔር ዓላማ እንድናከናውን ያደርጋል። እግዚአብሔር እኛን የወደደን ኢየሱስ ስለእኛ ስለሞተ አይደለም። ኢየሱስ የሞተልን እግዚአብሔር እኛን ስለወደደ ነው። ዮሐንስ 3:16 የሚያስታውሰን እግዚአብሔር ስለወደደን ልጁን እንደሰጠን ነው። እግዚአብሔር ኢየሱስን የሰጠን እኛን ለማዳን፤ እንጂ ሊፈርድብን አይደለም (ዮሐንስ 3:17)።

   በሁሉም ስፍራ የሞኖሩ ሰዎች በህይወታቸው ዓላማን እና ትርጉም ያለው ኑሮን መኖር ይፈልጋሉ። እነርሱም፤ " የእኔ ህይወት ዓላማ ምንድነው?" እያሉ ይጠይቃሉ። ይህ አለም አቀፍ ጥያቄ ነው። "ከመብላት፤ ከመጠጣት፤ እና ከመጋባት" ያለፈ ታላቅ ዓላማ እንዲኖረን እንናፍቃለን። በዚህ ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ከእርሱ ዓላማ ጋር የእኛን ዓላማ ያገናኛል። አባቱ ኢየሱስ ፍቅር፤ ይቅርታ እና ሰላምን ወደ ዓለም እንዲያመጣ እንደላከው ሁሉ ኢየሱስ ደግሞ ለተመሳሳይ ዓላማ ወደ ዓለም ልኮናል። በቤቴ ይሁን በስራ ቦታ፤ በሰፈር ይሁን በመንገድ ላይ ሰዎችን ይቅር የምል እና ፍቅርን እና ሰላም የሚያመጣ ሰው እሆናለሁ። ይህ ታላቅ አላማ ነው! ይህ ለህይወት ትርጉም ይሰጣል። ይህ *ዘላለማዊ ዋጋ* አለው።

**ትግበራ**:

1. ከእነዚህ ስጦታዎች የትኛዎቹ ናቸው ለእናንተ ውድ የሆኑት?

   ________________________________________

   ምክምያቱም

   ________________________________________

   ________________________________________

2. ከትንሳኤው ጌታ የተቀበልኳቸውን እነዚህን ስጦታዎችን ማወቅ በእርሱ እቅድ መሰረት በእርሱ ተልዕኮ ላይ እንድሳተፍ እና ውጤታማ እንድሆን ምን ያህል ይረዳኛል?

   ሀ. የእርሱ ሰላም ስጦታ:

   ________________________________________

   ________________________________________

ለ. የእርሱ እቅድ ስጦታ:

____________________________________________________

____________________________________________________

ሐ. የእርሱ ሃይል ስጦታ:

____________________________________________________

____________________________________________________

መ. የእርሱ ዓላማ ስጦታ:

____________________________________________________

____________________________________________________

**ፀሎት**

ራሳችሁን በጌታ ፊት በፀሎት ቅረቡ። እናንተ ጠቃሚና አስፈላጊ ሰዎች እንድትሆኑ እና ህይወታችሁ ትርጉም ያለው እንዲሆን ስላደረገው ስጦታው እግዚአብሔርን አመስግኑት። የእርሱን ስጦታ በመጠቀማችሁ እና ስለእርሱ ምሪት እና መመሪያ አመስግኑት። እነዚህን ስጦታዎች በታላቅ ዓላማ እንድትጠቀሙ እና ለእርሱ ክብር የሚሆንን ነገር ማድረግ እንድትችሉ እንድትረዱ እና የሰዎች ህይወት በእርሱ ስጦታ መባረክ እንድትችሉ ፀልዩ።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

___________________________________________________________

# ትምህርት ስድስት

# ትወደኛለህ?

## ዮሐንስ 21:1-19 — ተከተለኝ

---

**የትምህርት 6 ምልከታ**

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 6: ዮሐንስ 21:1-19

- አሳ ወደ ዓሳ ማጥመድ መሄድ
- ማሰላሰል እና ትግበራ
- የሚገርም ነው! ብዙ ዓሳዎች!
- ያላለቀ ሥራ
- ኢየሱስ ላይ ያተኮሩ ዓይኖች

## መግቢያ

ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ እንዳዘዛቸው እስከ ገሊላ ድረስ ሄደዋል። እነዚህ ሰዎች የተሰላቹ ይመስላሉ። በዮሐንስ 21 ላይ እንደምንመለከተው ወደ ዓሳ ማጥመዳቸው ለመመለስ ወሰኑ። ከዚያስ ምን ሆነ? የእነርሱን ዓሳ መያዝ እና የእግዚአብሔር ህዝብ የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ስራን እንደ ምሳሌ አድርጋችሁ አነፃፅሩ። የእነርሱ ዓሳ ማጥመድ ለተጠሩለት የሰዎችን ማጥመድ ስራ ምንድነው የሚያስተላልፈው መልዕክት?

"እግዚአብሔር እኔን ይጠቀማል?" ብላችሁ ጠይቁ። ነገር ግን በትክክል ሊናውቀው የሚገባን ነገር ፤ "እግዚአብሔር እንዳይጠቀምብኝ ማለትም አሁን እና ወደፊት ያደረኩት እና የማደርገው መጥፎ ነገር አለን?" የሚለውን ነው። ጴጥሮስ ጌታውን የካደው በፍፁም አደርገዋለሁ ብሎ አስቦት፤ አልሞትም የማያውቀውን ነው። ነገር ግን ጌታን ከካደው በኋላ ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ። ይቅርታን ወዲያው አገኘ። እግዚአብሔር ይቅርታ ሲያደርግ ወዲያውኑ ነው። ኢየሱስ ሌላ መፈታት ያለበት ነገር እንዳለ ያውቃል። በክፍል 6 ከኢየሱስ አጠገብ ፀጥ ብላችሁ ተቀመጡና እርሱ ከጴጥሮስ ጋር ያደረገውን ንግግር አድምቱ። በዚህ ውይይት ውስጥ ለጥያቄአችሁ ከኢየሱስ መልስ ታገኙ ይሆናል።

# ትምህርት 6

## <u>ምዕራፍ 1</u>

### *መግቢያ*

*ይህ ቀጣዩ ታሪክ በእግዚአብሔር ፍቅር፣ የእኛ ህይወት* በሚለው ጥናት ውስጥ ቆየት ብሎ የሚቀርብ ነው። አብዛኛው ታሪኩ የሚያውጠነጥነው በዓሳ ማጥመድ፤ በዓሳ፤ እና በዓሳ አጥማጆች ላይ ነው። ኢየሱስ እንዲህ አለ፤ " ተከተለኝ፤ አሳ አጥማጅ አደርግሃለሁ።" ኢየሱስ አገልግሎቱን ሲጀምር አሳ አጥማጆችን በእነዚህ ቃላት በመጥራት ነው። ይህንኑ ተመሳሳይ ቃል "ተከተለኝ" የሚለውን በዮሐንስ 21 ላይ በድጋሚ እናገኛለን።"

**የቤት ስራ**: ዮሐንስ 21:1-14 አንብቡት።

**መልመጃ**:

1. ይህ ታሪክ የተከናወነው የት ነው (ቁጥር 1)?

   ______________________________________________

2. በዚያ ስፍራ የተሰባሰቡት እነማን ናቸው (ቁጥር 2)? ______________________________

   ______________________________________________

3. ጴጥሮስ ምን ሊያደርግ ነው (ቁጥር 3)?

   ______________________________________________ ሌሎቹስ ምን አሉ

   ______________________________________________

4. በዚያን ሌሊት የዓሳ ማጥመድ ስራው እንዴት ነበር?

   ______________________________________________

5. በነጋታው በማለዳ ኢየሱስ በሐይቁ ዳርቻ ቆሞ ነበር። ስለደቀ መዛሙርቱ የተነገረን ነገር ምንድነው (ቁጥር 4)?

   ______________________________________________

6. ኢየሱስ ጠራቸው እና

   "______________________________________________::"

7. በእርግጥ ምንም ዓሳ አልያዙም ነበር፤ ኢየሱስ ግን ምን አድርጉ አላቸው (ቁጥር 6ሀ)?

   ______________________________________________

8. ውጤቱም (ቁጥር 6ለ):

   ______________________________________________

________________________________________________________________

9. ቀድሞ ኢየሱስን ያወቀው ማነው (ቁጥር 7)? _____________________________________
   ጴጥሮስን፡፡ ____________________ አለው፡፡ "
10. ጴጥሮስ ወዲያውኑ የወሰደው እርምጃ ምንድነው (ቁጥር 7ለ)?

    ________________________________________________________________
11. ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ምን አደረጉ (ቁጥር 8)?

    ________________________________________________________________

    ________________________________________________________________
12. ከሃይቁ ላይ ወደ ዳርቻው ሲደርሱ ቀድሞ የተዘጋጀላቸው ነገር ምንድነው (ቁጥር 9)?

    ________________________________________________________________

    ________________________________________________________________
13. ምን እንዲያደርጉ ነው ኢየሱስ የጠየቃቸው (ቁጥር 10)?

    __________________________________________
14. ጴጥሮስ ወደ ጀልባይቱ ገብቶ አሳ የያዘውን መረብ ወደ መሬት ጎተተው፡፡ ስለዚህ ነገር ክፍሉ ምን ይላል (ቁጥር 11)?
    
    ሀ. ____________________________________________________________
    
    ለ. ____________________________________________________________
15. ኢየሱስ ____________________ ጠየቃቸው ______________________ ጋበዛቸው፡፡
16. ከደቀ መዛሙርቱ _______________ አንተ ማን ነህ? ብሎ _______________ አልነበረም፤ _______________ መሆኑን አውቀው ነበርና (ቁጥር 12)፡፡
17. ኢየሱስ ዓሳው እና እንጀራውን ምን አደረገው (ቁጥር 13)?

    ________________________________________________________________

    ________________________________________________________________

***ምዕራፍ 2***

**ማሰላሰል**:

1. በእነዚህ ጥቂት ቁጥሮች ውስጥ ጴጥሮስን መመልከት ያስደስታል፡፡ መልአኩ መቃብር ጋ እንዲሁም ኢየሱስ ለሴቶቹ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ገሊላ እንዲሄዱና እርሱን እንዲጠብቁት እንዲነግሯቸው ተናግረው ነበር፡፡ ኢየሱስ በገሊላ ተገለጠላቸው ነገር ግን ጴጥሮስ ተሰላችቶ እና ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ጋር ያለስራ ተቀምጦ እናየዋለን፡፡ ያለስራ መቀመጥ እና መጠበቅ ከባድ ነው ስለዚህም ጴጥሮስ አሳ ለማጥመድ ወሰነ ሌሎቹም እንደእርሱ ለማድረግ ወስነው

ከእርሱ ጋር ሄዱ። ስለእርሱ የምናነበው ቀጣዩ ነገር ከጀልባዋ ላይ ዘልሎ እየዋኘ ወደ ኢየሱስ መሄዱን ነው! ከዚያ ቀጥሎ ደግሞ ወደ ጀልባዋ ተመልሶ በመውጣት በበርካታ አሳዎች የተሞላውን መረብ ወደ ምድር ጎተተው። እርሱ በሃይል ተሞልቶ ሊፈነዳ የደረሰ ይመስላል! ነገሩ የሚመስለው ለኢየሱስ የሚገባውን ነገር እንደሚገባው እርሱ እንዳላደረገ ነው…ወይም…ገና ያልተፈቱ ነገሮች ስላሉ በኢየሱስ አካባቢ ለመሆን ደስተኛ ያልሆነ ይመስላል። ጴየጥሮስ ጌታውን የካደውን ሁኔታ እያሰባችሁ አሁን በእርሱ አዕምሮ ውስጥ ምን አይነት ሃሳብ የሚመላለስ ይመስላችኋል? የእናንተ አስተያየት ምንድነው:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

2. አሳ አጥማጁን ጴጥሮስ ለአጭር ጊዜ ተመልክተነዋል። በተዓምር ስለተያዙት ዓሳዎች የእናንተ ሃሳቦች ምንድናቸው (ቁጥር 6) እንዲሁም ስላልተቀደደው መረብ ምን ትላላችሁ (ቁጥር 11)? ይህንን ለማመን ከባድ ነው? ይህ ጉዳይ የታሪኩ ዋና ነገር ነው? እንዴት ነው ይህ የዓሳው እና የመረቡ ታሪክ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ልብ፤ ያም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ እንዲመጡና እርሱን እንዲያውቁ፤ በእርሱ ፍቅር እንዲታቀፉና ወደ እርሱ መንግስት ፤ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመጡ ምሳሌ መሆን የሚችለው? በመረቡ የተያዙት የአሳዎች መጠን ሰዎቹ ከገመቱት እጅግ ይበልጣል፤ ምንም እንኳን ከፍተኛ የሆነ አሳዎች ወደ መረቡ ቢገቡም መረቡ አልተቀደደም። ኢየሱስ ምን እያደረገ ነው? ዋናው ዓሳ አጥማጅ እነርሱን ምን እያስተማራቸው ነው? ቀላል በሆነ መመሪያ መረባቸውን ወደ ተነገራቸው አቅጣጫ መጣላቸው ምንድነው የሚያመጣው ለውጥ? እንዴት አድርገን ነው ከኢየሱስ ጋር ተባብረን መረባችንን ለኢየሱስ ዓሳዎችን ማምጣት እንደሚችል አድርገን ወደ ባህር የምንጥለው (ቁጥር 10)? እንዴት አድርገን ነው ከኢየሱስ እና ከሌሎች ጋር ተባብረን ዓለም ወደ እርሱ መረብ ማስገባት የምንችለው? የእናንተ ሃሳቦች:

________________________________________________________________

________________________________________________________________

________________________________________________________________

**ትግበራ**:

1. ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ “መረባችሁን ጣሉ…” ሰዎችን እንደሚያጠምድ ሰው ምን ዓይነት መረብን ነው ሰውን ለማጥመድ የምንጠቀመው?

________________________________________________________________

2. መረቤን የት ነው የምጥለው? በእኔ ቤት ነው? በጎረቤቶቼ ላይ ነው? መኪናዎች እና ሰዎች በሚበዙበት አካባቢ ነው? ዓሳዎቹ የት ነው ያሉት?

________________________________________________________________

3. ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፤ "ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ አላቸው" እናንተ ዓሳ አጥማጅ ናችሁ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ፍቅር የምታደምዱ! እስቲ ታሪካችሁን ለሌሎች ሰዎች አካፍሉ። ኢየሱስ እናንተ ስለያዛችሁት ዓሳ መስማት ይፈልጋል! የእናንተ የአሳ ወጥመድ ውስጡ ምንድነው ያለው? ወዴት ነው የሄዳችሁ? መረብን ትጠቀማላችሁ?

_______________________________________________

_______________________________________________

4. ወደ ዓሳ ማጥመዱ ከእናንተ ጋር እንዲያጠምድ ማንን ነው የምትጋብዙት? እናንተን ሰዎች የሚከተሉ ከሆነ ከእናንተ አሳ ማጥመድን ይማራሉ? ከእናንተ እንዲማሩ ምንን ነው የምታሳዩአቸው?

_______________________________________________

_______________________________________________

## <u>ምዕራፍ 3</u>

### መግቢያ

ኢየሱስ ከጴጥሮስ ያልጨረሰው ጉዳይ አለው ። ነገሮች ገና ሙሉ በሙሉ አልተፈቱም። ጴጥሮስ ያለጥርጥር ይቅር እንደተባለ ያውቃል። ኢየሱስ በትንሳኤው እለት ለእርሱ እንደተገለጠ እናውቃለን (ሉቃስ 24:34) ከጌታ ትንሳኤ ጋር ተያይዞ ጴጥሮስን ያስደነቀው ነገር ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያቅትም (ሉቃስ 24:12) ። ነገር ግን ገና ያልተመለሰ ጥያቄ አለ፤ "ኢየሱስ በጣም ስለበደልኩህና ኃጢአትን ስለሰራሁ ከአሁን በኋላ በእኔ አትጠቀምም ማለት ነው?"

**የቤት ስራ**: ዮሐንስ 21:15-19 አንብቡት

**መልመጃ**:

1. ቁርሳቸውን በልተው እንደጨረሱ ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር መነጋገር ጀመረ ጴጥሮስ። ጴጥሮስን ምን ብሎት ጠየቀው (ቁጥር 15)?

_______________________________________________

2. ጴጥሮስም እንዲህ ብሎ መለሰለት፤
"_______________________________________________።"

3. ኢየሱስ መልሶ፤
"_______________________________________________።"

4. ቁጥር 16 እና 17 ላይ ያለው በቁጥር 15 ላይ ያለው የተደገመበት ነው። ትወደኛለህ? አንተ ታውቃለህ። በጎቼን መግብ። ጴጥሮስ ኢየሱስን ሶስት ጊዜ ካደው አሁን ደግሞ በተራው

ኢየሱስ ጴጥሮስን ሶስት ጊዜ ተመሳሳይ ጥያቄን ጠየቀው፤ ለጴጥሮስም ተመሳሳይ መመሪያን ሰጠው። ምሳሌው ተቀየረ። ዮሐንስ የተናገረው ስለ አሳ ማጥመድ ታሪክ ነው፤ ነገር ግን ኢየሱስ ____________________ ነው የሚናገረው። " ____________________ መግብ።"

5. ከዚያ በኋላ ቁጥር 18 ላይ ኢየሱስ ጴጥሮስ ሲያረጅ ምን እንደሚደርስበት ተናገረው:

   ሀ. ጴጥሮስ ጎልማሳ እያለ ምን እንደሚያደርግ ነው ኢየሱስ የተናገረው

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

   ለ. ጴጥሮስ ሲያረጅ ምን ይገጥምሃል ብሎ ኢየሱስ ተናገረው?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

6. ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ ሞት ሲናገር መስማት ደስ ይላል። ኢየሱስ የራሱን ሞት እንደተናገረ ሁሉ ስለ ጴጥሮስ አሟሟትም ተናገረ። ኢየሱስ ስለ ጴጥሮስ ሞት ሲነገር ______________________________ (ቁጥር 19) እንደሆነ ነው።

   *ማስታወሻ:* የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚናገረው ጴጥሮስ እና የእርሱ ሚስት ሁለቱም በስቅላት የተገደሉ ሲሆን ጴጥሮስ ግን የተሰቀለው ጭንቅላቱን ወደ ታች ተዘቅዝቆ ነው። የዚህን አይነት አሟሟት እግዚአብሔርን ያስከብራ ብሎ ማሰብ ከባድ ነው፤ ነገር ግን የኢየሱስ ቃላት በእምነት እንቀበላለን።

7. ከዚያም ኢየሱስ ጴጥሮስን ከሶስት አመት በፊት ሲጠራው በተጠቀመው ተመሳሳይ ቃላት በድጋሚ ለአገልግሎቱ ሾመው፤ ማቴዎስ 4:20። "______________ ________።" ጌታ የጴጥሮስን ልብ ያውቃል። ጴጥሮስ እንዴት እንደካደው ያውቃል። ጴጥሮስ በሰራው ጥፋት እንደተፀፀተ እና ንስሃ እንደገባ ያውቃል። እርሱ ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ እንዳለቀሰ እርሱ ያውቃል (ሉቃስ 22:62)። ጴጥሮስ ግን በኢየሱስ ዘንድ ተፈላጊ መሆኑን ማወቅ ይፈልጋል። ኢየሱስ ነገሮችን በጣም ግልፅ አድርጓል። " ጴጥሮስ፤ተከተልኝ፤እስከ መስቀል ሞት ድረስ፤ እኔ የምነግርህ ህያው ሆነህም ሆነ ሞተህ እግዚአብሔርን ታከብራለህ።"

<u>ምዕራፍ 4</u>

**ትግበራ**

እኛም እርሱን ስንከተል አይናችንን በኢየሱስ ላይ እንድናደርግ ተነግሮናል። ዕብራውያን 12:2 እንዲህ ይላል፤ "የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፤ እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ

ተቀምጦአልና። ስለጴጥሮስ በዚህ ታሪክ ውስጥ ( ዮሐንስ 21) እና ስለ ኢየሱስ እና ስለ መስቀል ( ዕብራውያን 12) ከተመለከተነው አንፃር “የራሴብ አይኖች በኢየሱስ” ላይ ትኩር አድርጌ እርሱን ለመከተል ጥሪት አደርጋለሁኝ።

1. እኔ ከእርሱ ጋር ወዳጅ ነኝ ካልኩኝ ይህ ለእኔ ምን ማለት ነው?

 ______________________________________________

2. የራሴን ህይወት ዘይቤ ሳስብ ይህ ለእኔ ምን ማለት ነው?

 ______________________________________________

 ______________________________________________

3. የእኔ መስቀል መስቀል ሳስብ ይህ ለእኔ ምን ማለት ነው?

 ______________________________________________

 ______________________________________________

**ማሰላሰል**:

1. ሉቃስ በሌሎች ወንጌላት ውስጥ ያልተዘገቡትን ነገሮች ይነግረናል፡ in በሉቃስ 22:31-32 ውስጥ ለኢየሱስ ጴጥሮስ ምን ብሎ ነው የተናገረው?

 ______________________________________________

 ______________________________________________

 ______________________________________________

2. ይህንን ክፍል ከዮሐንስ 21:15-17 አንፃር ተመልከቱት። ኢየሱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ተናገረው:

 ሀ. ቁጥር 15: ______________________________

 ለ. ቁጥር 16: ______________________________

 ሐ. ቁጥር 17: ______________________________

 ጴጥሮስ ለኢየሱስ ያለውን ፍቅር ወንድሞቹን በማበረታታት እንዲገልፅ ተጠየቀ(ሉቃስ 22:32)።

3. ጴጥሮስ ኢየሱስን ከመካዱ አንፃር፤ ይህ የእርሱ የህይወት ልምድ ማለትም ኢየሱስን መካዱና እና ይቅርታን ከኢየሱስ መቀበሉ ወንድሞችን ከማበረታታት አንፃር ምን ዓይነት ትርጉም ይኖረዋል?

 ______________________________________________

 ______________________________________________

4. በእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚኖር ሰው መኖራችሁን ከአወቃችሁ፤ የእናንተ የራሳችሁን ድካም እና ውድቀትን እግዚአብሔር እንዴት ተጠቅሞበት ነው ሌሎችን የሚያበረታታው?

 ______________________________________________

 ______________________________________________

**ማስታወስ**: ኢየሱስ ስለበጎች በተጨማሪ ተናሯል ዮሐንስ 10:3ለ-4። "በጎቹ ድምፁን

____________________________________________________________

__________________________________________________________።"

ስለ እግዚአብሔር ቃል በበለጠ ለማወቅ ለሚጓጉ ሁሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ሐዋሪያው ጴጥሮስ እራሱ በትንሽዋ እስያ ማለትም በዘመኑ ቱርክ በምትባል አገርለ ለነበሩ ቤተ ክርስቲያናት በፃፈው ደብዳቤ እኛን ያበረታታናል። በ1 ጴጥሮስ 5:2 የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ብሎ ያፅናናል: "በእናንተ ዘንድ ያለውን ________________________________፤ እንደ ____________________ፈቃድ በውድ እንጂ ____________________፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ ____________________በመመኘት ሳይሆን ጒብኙት።"

**ፀሎት**

ጌታ ኢየሱስ ሆይ አሁንም እንደገና "ተከተለኝ " ያልከውን ያንተን ድምፅ እሰማለሁ። በጎቼን መግብ ብለኸኛል፤ በዚህም በጎችህ ድምፅህን ስለሚሰሙ አንተን ይከተላሉ ። የእኔ አንተን ስከተል አይኖችን በአንተ ላይ በማድረግ በአገልግሎቴ ታማኝ እሆን ዘንድ እርዳኝ። ስስት እና ከመንገድህ ስወጣ እጄን ያዝ፤ እኔን ተንከራታቹን በግ አድሰኝ። ኢየሱስ በትህትና በፊትህ ሆኔ ከአንተ ውጭ ምንም ማድረግ እንደማልችል አውቃለሁ እና ሁሉጊዜ እርዳኝ። መረቤን አሳዎች ወደአሉበት ቦታ እንድጥል እና ሰዎች ወደ አንተ መንግስት እና ቤተክርስቲያን እንዲጨመሩ እና በአንተ የትንሳኤ ሃይል እንዲድኑ እንዳደርግ አበረታታኝ።

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

# ትምህርት ሰባት

# ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ

## ማርቆስ 16 — የኢየሱስ ትዕዛዝ

---

**የትምህርት 7 ምልከታ**

ምልከታ

መግቢያ

ትምህርት 7:  ማርቆስ 16

- በአብ ቀኝ
- ለማመን እምቢ ማለት
- የኢየሱስ ማረግ
- የኢየሱስ መመሪያ
- የምልክት ቁጥሮች

## *መግቢያ*

*ኢየሱስ አሁን የት ነው ያለው? ደመና ሰውራ የወሰደችው ይመስላል። እርሱ በፍፁም እንደማይተወን እና እንደማይጥለን ተናግሯል። ታዲያ እርሱ የት ነው ያለው? የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ወደ ላይ ወደ ደመና በመመልከት አሸናፊው መሪያቸው ምን እንደሆነ እንደፈለጉት ሁሉም እኛም ተነሳሳይ ስሜት ሊሰማን ይችላል። እርሱ ወዴት ነው የሄደው?*

*ትምህርት* 7 *ይህንን የዓለም አዳኝ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ህይወት፣ ሞት፣ እና ትንሳኤ ጥናትን የምናጠናቅቅበት ነው፡ ሁሉም የመፅሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ወደዚህ ታላቅ ታሪካዊ ክስተት የሚያመለክቱ ናቸው። የብሉይ ኪዳን መፃህፍት ስለተቀባው፣ ስለ መሲሁ፣ ስለክርስቶስ፣ ህዝቡን እንድቤዤ በእግዚአብሔር ቃል ስለተገባው አዳኝ የሚናገሩ እና ስለመምጣቱ የሚተነብዩ ናቸው፡ አዲስ ኪዳን ደግሞ ስለዚህ አዳኝ መወለድ፣ መሰቀል እና መቃብሩ ባዶ መሆን ማለትም ስለየኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ ከመሰከሩ በኋላ በእርሱ ስምናገኘው የዘላለም ህይወት፣ሰላም እና ደስታ ይናገራሉ። እኛ ይህንን ሁሉ ያደረገ አዳኝ አለን። እኛ በራሳችን ሃይል ማድረግ የማንችለውን እርሱ አደረገልን። እርሱ እኛን የተቤዠን ውድ በሆነው ለኃጢአታችን ይቅርታ በፈሰሰው የመስዋዕት ደሙ እና በተገረፈው ሰውነቱ ነው።*

# ትምህርት 7

## ምዕራፍ 1

### መግቢያ

ከዚህ በፊት ተነግሮ የማያውቅ ከዚህም በኂላ ሊነገር የማይችልን እጅግ ታላቅ ታሪክን ሰምተናል። ከአራቱ ወንጌላት ሶስቱ ተጨማሪ ታሪኮችን ይዘዋል። ማቴዎስ፤ ማርቆስ፤ እና ሉቃስ በኢየሱስ ላይ ምን እንደደረሰበት ይናገሩናል። ሁሉም በላይ እንደሞተ አልቀረም ከሞት ተነስቷል። ከሞት ከተነሳ በኂላ ራሱን ለብዙ ሰዎች በተለይም ለእራሱ ደቀ መዛሙርት እና ለተከተሉት ሰዎች ህያው መሆኑን አሳይቷቸዋል። ነገር ግን አሁን እርሱ የት ነው ያለው? እርሱ ህያው ሆኖ የሆነ ቦታ ነው ያለው? ምን ደረሰበት? እስቲ ወንጌላት የሚናገሩትን እንስማ።

### ትምህርት

ወደ ኂላ ተመልሰን አንዳንድ ነገሮችን እንመልከት። ኢየሱስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት የተከሰሰበትን ሂደት ከማቴዎስ 26:63-64 እንመልከት። ሊቀ ካህናቱም። አንተ ________________________የሆንህ እንደ ሆነ እንድትነግረን በሕያው ________________________ አምልሃለሁ አለው። ለዚህ ጥያቄ የኢየሱስ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 64ሀ)?

______________________________________________________________________________

ኢየሱስ በቁጥር 64 ላይ ቀጥሎ ትንቢት ተናገረ።ለሁሉም ሰዎች የተናገረው ነገር ምንድነው?

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ኢየሱስ የጠቀሰው ይህ “ሃይል” ማነው? ማርቆስ 16:19 ተመልከቱ።

____________________________________

ይህ ምን ማለት ነው፤ ኢየሱስ በዚህ ሃይል ቀኝ መቀመጥን ይፈልጋል ማለት ነው? በዚህ ሃይል ቀኝ መቀመጥ የሚያሳየው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ድምፅ እንደነበረ ነው። ዮሐንስ በዮሐንስ 1:1፤ 2 ላይ የተናገረውን አስታውሱ። ዮሐንስ ስለኢየሱስ ሲናገር “__________________ ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ __________________አደረ፥ አንድ ልጅም __________________ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው __________________ አየን።”

በሃይል ቀኝ መቀመጥ ለልጅ፤ለልዑል እና ለአባት የበኩር ልጅ ብቻ የሚፈቀድ ነው። ይህ የሃይል ቀኝ የአገዛዝ እና የስልጣን ቦታ ነው። እንደ ኤፌሶን 1:19-21 ኢየሱስ ያለው ስልጣን ምንድነው?

_______________________________________________________________________

_______________________________________________________________________

ከሚከተሉት የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ እግዚአብሔር ቀኝ ተጨማሪ ትምህርት የምናገኘው ምንድነው?

ሀ. ሮሜ 8:34? ______________________________________________

ለ. ዕብራውያን 1:3ለ-4? ______________________________________________

መ. ዕብራውያን 12:2? ______________________________________________

**የቤት ስራ**: በማርቆስ 16:9-16 ላይ የተጠቀሰውን ታሪክ አንብቡና የኢየሱስ ትንቢት መፈፀሙን አጢኑት። ማርቆስ በፋሲካ በዓል እና ከዚያ በኋላ የሆነውን በአጭሩ ይከልሳል። ይህ ክፍል ሁለቱ ወንጌላት ስለትንሳኤው የተናገሩትን ያጠናክራል፤ ተጨማሪም ሀሳቦችን ይሰጠናል።

**መልመጃ**:

1. ኢየሱስ ከሞት እንደተነሳ ቀድሞ ለማን ነው የተገለጠው (ቁጥር 9)?

   ___________________________

2. ስለእርሷ የተነገረን ነገር ምንድነው?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

3. ኢየሱስን ከተመለከተችው በኋላ ለማን ነው የነገረችው (ቁጥር 10ሀ)?

   ______________________________________________________________

4. እነርሱ እንዴት ነው የተገለጡት (ቁጥር 10ለ)?

   ______________________________________________________________

5. ማርያም ስላመጣችው የምስራች የእነርሱ ምላሽ ምን ነበር (ቁጥር 11)?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

6. ማርቆስ የሚነግረን ወደ ___________________________ ስለሚጓዙ ሰዎች ነው።

   ሉቃስ 24:13 - ተመልከቱ። እነርሱ የተናገሩት ነገር ምንድነው?

   ______________________________________________________________

   ______________________________________________________________

7. ለሰሙት ነገር ደቀ መዛሙርት የሰጡት ምላሽ ምን ነበር (ማርቆስ 16:13)?

______________________________________________

______________________________________________

8. ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ኢየሱስ ለማን ነው የተገለጠው (ቁጥር 14)?

______________________________________________

9. ኢየሱስ እነርሱን የገሰፀው

ለ______________________________________________ እና

______________________________________________

10. ምንም እንኳን ለማመን ፈቃደኛ ባይሆኑም ኢየሱስ ምንድነው የተናገራቸው (ቁጥር 15-16)? "እንዲህም አላቸው፦ ወደ ____________ ሁሉ ሂዱ ____________ ለፍጥረት ሁሉ ____________ ።የመነ ____________ ይድናል፥ ____________ ግን ይፈረድበታል።። ።"

<u>ምዕራፍ 2</u>

**ማሰላሰል**: ለአጭር ጊዜ እረፍት እናድርግና በተወሰኑ ነገሮች ላይ እናሰላስል።

1. ደቀ መዛሙርቱ በእንባ፤በለቅሶ እና በሃዘን ውስጥ ስለነበሩ ማርያም እና ሌሎቹ ሴቶች ከነገሯቸው ታላቅ የምስራች፤ የኢየሱስ ከሞት መነሳት እና ህያው መሆን ሰበር ዜና ይልቅ እነርሱ የመረጡት በሃዘናቸው መቀጠልን ነው። እርሱ ተነስቷል! እነርሱ ግን ____________________ ።
2. ወደ ኤማሁስ ይሄዱ የነበሩት ሁለት ሰዎች ኢየሱስን አግኝተውታል። አይኖቻቸው በተከፈተ ጊዜ ኢየሱስ መሆኑን አውቀውታል፤ ወደኋላም ተመልሰው የኢየሱስን ህያው መሆን በኢየሩሳሌም ከአይሁድ ፍርሃት የተነሳ ተደብቀው ላሉት ደቀ መዛሙርት ለመናገር ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። እነርሱ አይተውታል። እርሱ ተነስቷል! የማርቆስ ወንጌል እንደሚናገረን፤ ደቀ መዛሙርቱ ______________________________ ።
3. ኢየሱስ አስራ አንዱ እየተመገቡ እያለ ተገለጠ። ኢየሱስ ሴቶች ለእርሱ ደቀ መዛሙርት እርሱ ከሞት እንደተነሳ እንዲነግሯቸው እንደፈለገ አስታውሱ (ማቴዎስ 28:9-10)። ትንሳኤውን ለማወቅ እነርሱ የመጀመሪያዎቹ ናቸው። ይልቁንም ለዚህ ታላቅ ዜና የሰጡት ምላሽ ባለማመን ነበር። ኢየሱስ ለምንድነው የገሰፃቸው?

   ሀ. ______________________________________________

   ለ. ______________________________________________

በዚህ ዘመን ከግትርነታቸው የተነሳ አላምንም ያሉትን ሰዎች ተመሳሳይ ነገር ቢነግራቸው ምን የሚደንቅ ነገር አለ። በዚህ ላይ የእናንተ ሃሳቦች ምንድናቸው:

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

**ትግበራ**

ኢየሱስ እራት ሊበላ ወደ እናንተ ቤት ቢመጣ፤ እናንተን ሰዎች ስላዩት እና ስለሰሙት ነገር ሲመሰክሩላችሁ ከግትርነታችሁ የተነሳ ባለማመናችሁ ምክንያት ይገስፃችኋል? ለም? የማይገስፃችሁ ከሆነ ደግሞ ለምን?

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

**ማስታወስ**

ማርቆስ 16:15-16 ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የተናገራቸውን ቃላት ይዘግባሉ። በዚህ ስፍራ ትዕዛዝ አለ፤ እርሱም "ሂዱ" የሚል ነው። ትዕዛዙ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ የሚል ነው። ይህ ትዕዛዝ ወደ ዓለም ሁሉ ሄዶ የምስራቹን ቃል ለፍጥረት ሁሉ መስበክ ነው። ትዕዛዙ የተስፋ ቃልን የያዘ ነው፤ ተስፋውም ማንም የአመነ የተጠመቀም እንደሚድን የሚናገር ነው። ደግሞም "____________________________ ግን ይፈረድበታል" ይላል። አለማመን ፍርድን ያመጣል። በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ያላመነ ሁሉ ይፈረድበታል።

እነዚህን ቁጥሮች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ፃፏቸው። እነዚህ በኢየሱስ የተነገሩ ቃላት ብናምን እንደምንድን ያረጋግጡልናል። የዘላለማዊ ህይወትም ይሰጠናል። ይህንን ታላቅ የምስራች ሁልጊዜ አስታውሱት፤ ለዎችም ሁሉ አካፍሉት!

**ፀሎት**

ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ ከሞት በእርግጥ እንደተነሳህ እንዳመን እባክህ እምነትን ስጠኝ። አንተ ህያው እንደሆንክ እኔም ህያው እንደምሆን አምን ዘንድ እምነትን ስጠኝ። ይህ የምስራች ለእኔ ድነትን ብቸኛው አማራጭ እንደሆነ እንዳምን እርዳኝ። ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ የምስራቹን ቃል ኢየሱስ ሰዎች የህይወታቸው ጌታ እና አዳኝ እንደሆነ እንድመሰክር እርዳኝ።

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

____________________________________________________________________________

## ምዕራፍ 3

### መግቢያ

የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ስንመለከት ስለእምነት በርካታ ጊዜ ተፅፏል። ለማርቆስ እምነት ምንድነው? ለእርሱ የትንሳኤው መልዕክት ዋና ሃሳብ ምንድነው? ትንሳኤ በፋሲካ ሰሞን የሆነ አንድ ክስተት ብቻ ነው? ለደቀ መዛሙርት እርሱን በደንብ ለሚያውቁ ነገሩ የሚያሳዝን ይመስላል። እነርሱ ኢየሱስን እንዲከተሉት የተጋበዙ ሰዎች ናቸው። እነርሱ ኢየሱስ 5000 ሺህ ሰዎችን ዓሳን እና እንጀራን በተዓምራት ሲያበላ አብረውት የነበሩ ናቸው። እነርሱ በኢየሱስ እግር ስር ቁጭ ብለው እርሱ ሲያስተምር ያዳመጡ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስ ማን እንደሆነ እንዲያምኑ ያደረጋቸው እምነት እንደሆነ የማይረዱ ይመስላችኋል? እነዚህን ሰዎች ኢየሱስ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ እና ጌታ እንደሆነ እንዲያምኑ ያደረጋቸው እምነት ነው። ከእነርሱ መካከል ግትር ሆነው ያላመኑ ሰዎች አሉ እንዴ? እነርሱ እምነት እንዲኖራቸው እና እንዲያምኑ የጠራቸው ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ የጠራቸው አለማመናቸውን ወደጎን በመተው የተነገራቸውን እውነተኛውን ነገር እንዲያምኑበት ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ባለማመናቸው ምክንያት አልተዋቸውም። እርሱ እስከ መጨረሻው ስለወደዳቸው ከሞት መነሳቱን እራሳቸው በአይናቸው እንዲያዩ ኢየሱስ ለአስራ አንዱ ተገለጠላቸው። ለቶማስ እንዲህ አለው (ዮሐንስ 20:29)፤

"ስለ____________________አምነሃል፤____________________የሚያምኑ____________________ ናቸው አለው።"

**የቤት ስራ**: ማርቆስ 16:17-18 አንብቡት።

**መልመጃ**:

1. ኢየሱስ የአመኑትን ምልክቶች ይከተላቸዋል አለ። እርሱም "በስሜ
   ሀ.________________________________________
   ለ.________________________________________
   ሐ.________________________________________
   መ.________________________________________
   ሠ.________________________________________"
2. በሐዋሪያት ሥራ መፅሐፍ እነዚህ ነገሮች ሲሆኑ እንመለከታለን። የአመኑትን ሰዎች የሚከተሏቸውን ምልክቶችን መመልከታችሁን ቀጥሉ። ከእነዚህ ጥቅሶች ጋር የተያያዙ ምልክቶች የትኞቹ ናቸው?

   ሀ. የሐዋሪያት ሥራ 5:16

   ________________________________________

ለ. የሐዋሪያት ሥራ 8:7

______________________________________________________________

ሐ. የሐዋሪያት ሥራ 16:18

______________________________________________________________

መ. የሐዋሪያት ሥራ 10:46

______________________________________________________________

ሠ. የሐዋሪያት ሥራ 19:6

______________________________________________________________

ረ. የሐዋሪያት ሥራ 28:3-5

______________________________________________________________

**ማሰላሰል**

1. እነዚህ ያላመኑ ሰዎች ሴቶቹ ሲነግሯቸው የሰሙ ተመሳሳይ ሰዎች ናቸው? ለማመን የዘገየ ልብ እያላቸውም ቢሆን ኢየሱስ ይጠቀምባቸው ይሆን? የእርሱን አገልግሎት እንዲወጡ ኢየሱስ ይጠቀምባቸው ይሆን? እነርሱ ምን ዓይነት ሰዎች ናቸው? ለእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ምን ዓይነት መምህር ወይም ረቢ ነው የራሱን አገልግሎት እንዲቀጥሉለት አምኖ የሚሰጣቸው? የእናንተ ምላሽ:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

2. ከእነዚህ ሰዎች መካከል የአመኑ ነገር ግን የተጠራጠሩ ይኖሩ ይሆንን፡፡ አስተያየታችሁ ምንድነው:

______________________________________________________________

______________________________________________________________

3. ምንም እንኳን በጣም የሚመሳሰሉ ቢመስልም ፤ በ“ማመን” እና “በእምነት” መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ጠቃሚ ነው፡፡ አንድ ሰው ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን ሊያምናቸው ይችላል፡፡ በኢየሱስ ላይ እምነትን ማኖር ግን ትክክል በሆነ ነገር ከማመን ይበልጣል፡፡ እምነት ማለት ግን ኢየሱስ ለሰው ልጆች ድነት ያደረገውን ተቀብሎ የራስ ማድረግ ነው፡ ክርስቲኖች “እምነቴ በኢየሱስ ነው” ሲሉ እነርሱ እያሉ ያሉት ለዘላለማዊ ህይወቴ፤ለድነቴ ሁለንተናዬን ለምታመንበት፤ ለሞተልኝ ለጌታ ኢየሱስ አሳልፌ ሰጥቼዋለሁ፤ ለዘላለሙ አይተወኝም አይጥለኝም ማለታቸው ነው፡፡ እምነት በእግዚአብሔር ይታመናል፡፡ የእናንተ አስተያየት:

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

4. ፍጥረት ሁሉ መስማት የሚገባውን የምስራች ቃል አስይዞ ኢየሱስ ወደ ዓለም ሁሉ ደቀ መዛሙርቱን ላካቸው፡፡ በድጋሚ "ያመነ የተጠመቀም ይድናል!" የሚለውን እናስታውሰው፡፡ ያመነ የተጠመቀም የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል፡፡ ጥምቀት የተመሰረተው በእግዚአብሔር ነው፡፡ ጥምቀት የተጀመረው እግዚአብሔር ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛን ልጆቹ የሚያደርገን የምንጠመቅበትን ስሙን ( አብ፤ ወልድ፤እና መንፈስ ቅዱስ ) በመስጠቱ ነው፡፡ በጥምቀት "ወደ ዓለም ሁሉ" እንድንሄድ ተሾመናል፡፡ በእርሱ ወደ እርሱ ተልዕኮ የተጋበዝን የእርሱ ልጆች ነን! የእናንተ አስተያየት:

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

<u>ምዕራፍ 4</u>

**የቤት ስራ**: ማርቆስ 16:19-20 እንደገና አንብቡ

**መልመጃ**:

1. ኢየሱስ ለእርሱ ደቀ መዛሙርት መናገሩን በፈፀመ ጊዜ ምን ተፈጠረ (ቁጥር 19)?

   ሀ.____________________________________________________________

   ለ. ____________________________________________________________

2. ሉቃስ በዚህ ላይ ይጨምራል፡፡ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከተናገረ በኋላ እስከ ________________አወጣቸው እጆቹንም አንሥቶ ________________(ሉቃስ 24:50)፡፡ ________________ ከእነርሱ ________________ ወደ ________________ ዐረገ፡፡

3. የሐዋሪያት ሥራ መፅሀፍም የተፃፈው በቅዱስ ሉቃስ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ በሐዋሪያት ሥራ 1:9 ላይ በተጨማሪ ይነግረናል፡፡ ከ9-11 ባሉት ቁጥሮች ላይ ምን የሚያስደስት ነገር አለ?

   ሀ. ይህንም ________________________እነርሱ እያዩት ________________አለ፤ ደመናም________________ሰውራ ተቀበለችው፡፡

   ለ. ቀጥሎ ምን ሆነ?

   ______________________________________________________

   ሐ. መልአኩ ደቀ መዛሙርትን ምን ጠየቃቸው?

   ____________________________________________________________________

   ____________________________________________________________________

መ. መላዕክቱ የነገሯቸው ነገር ምንድነው?

______________________________________________________________________

____________________________________________________________

4. በማቴዎስ 28:17 ላይ እንደተፃፈው ደቀ መዛሙርት ባዩት ጊዜ _________________________፡፡ ቀጥሎ የሚገርም ቃል አለ፤ "ግን _____________________ ነበሩ፡፡" ኢየሱስ ህይወቱን የሰጠው ለእነዚህ ለማያምኑና ለሚጠራጠሩት ሰዎች ላይ ነው? በእርግጠኝነት አናውቅም፡፡ ማርቆስ እና ሉቃስ የሚነግሩንን እኛ አናውቅም፡፡

ሀ. ማርቆስ 16:20 እንዲህ ይላል፤-

i. እነርሱም ወጥተው________________________ ሰበኩ፡፡

ii. ጌታም ___________________________________ ነበር

iii. በሚከተሉትም___________________________________________ ነበር፡፡

ለ. ሉቃስ 24:52-53 እንዲህ ይላልt

iv. እነርሱም _______________________

v. በብዙ ____________________ወደ ኢየሩሳሌም ______________፡፡

vi. ዘወትርም ______________________ እየባረኩ ___________________ ኖሩ፡፡

**ማሰላሰል**:

1. ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ባረካቸው፡፡ እነርሱም አመለኩት፡፡ እርሱም ትቷቸው ሄደ፡፡ እነርሱ ወደ ኢየሩሳሌም በታላቅ ደስታ ተመለሱ፡፡ እርሱ ስፍራን ሊያዘጋጅላቸው ሄደ (ዮሐንስ 14:2)፡፡ እነርሱ በቤተ መቅደስ ዘወትር እግዚአብሔርን እያወደሱ ተመላለሱ፡፡ ከዚህ በላይ የሚሆን ነገር ነበርን? የሚጎድል ነገር ነበር? ወደ የሐዋሪያት ሥራ 1:4 ተመለሱ፡፡ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠው ትዕዛዝ ምንድነው? "ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ____________________ እንዳይወጡ ____________________፥ ነገር ግን፡፡ ከእኔ የሰማችሁትን ________________ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፡፡"
እግዚአብሔር አብ የገባው የተስፋ ቃል ምንድነው? ዮሐንስ 14:25-26 ተመልከቱ፡፡ ኢየሱስ ተላላፎ ከመሰጠቱ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን እራት በላ፡፡ እነርሱ የሚጠብቁት እርሱ የገባው የተስፋ ቃል ምድነው?

1. እግዚአብሐር አብ የሚልከው ማንን?

______________________________________________________________

2. መንፈስ ቅዱስ የሚያደርገው ነገር ምንድነው?

_______________________________________________

_______________________________________________

3. ስለ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ 14:16 የተነገረን ነገር ምንድነው?

ሀ. ሌላ ስሙ ማነው?

______________________________

ለ. እርሱን እንዴት እናውቀዋለን (ቁጥር 17)?

i. ______________________________

ii. ______________________________

2. ለመረዳት ከባድ ቢሆንም ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእኛ ውስጥ ይኖራል። ለመረዳት ከባድ ቢሆንም ግን በእኛ ውስጥ የሚኖረውን የእግዚአብሔርን መንፈስ ማወቅ አለብን። የእርሱ ቃል ኪዳን በፍፁም እንደማይተወን እና እንደማይጥለን ነው። የእውነት መንፈስ ፤ ኢየሱስ እራሱ፤ ከእኛ ጋር እና በእኛ ውስጥ ይኖራል። ነገር ግን፤ የእውነት መንፈስ ገና አልመጣም። ለዚህም ነው እነርሱ ወደ ኢየሩሳሌም የተላኩት፤ በዚያም የእርሱን መምጣት መጠበቅ አለባቸው።

<u>ምዕራፍ 5</u>

**መግቢያ**

አንዳንድ ጊዜ ነገ ስለሚሆነው ነገር ቀርቶ ስለዛሬ እርግጠኛ መሆን የማይቻልበት ሁኔታ አለ። ነገሮች መች እንደሚሆኑና በየትኛው ቅደም ተከተል እንደሚሆኑ በትክክል ማወቅ አይቻልም። በተደጋጋሚ ከትንሳኤ በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ገሊላ እንዲሄዱና በዚያ እንደሚያገኛቸው ተናግሯል (ማቴዎስ 28:7፤ 10)። ኢየሱስ እነርሱን መች እንዳገኛቸው ለማወቅ ከባድ ነው። አንድ የምናውቀው ነገር ኢየሱስ ትንሳኤ በኋላ እስከ አረገበት ጊዜ ድረስ ለአርባ ቀናት በምድር ላይ መመላለሱን ነው። በእርገጠኝነት የት እና መቼ አረገ የሚለው በጣም አስፈላጊ ጉዳይ አይደለም። ኢየሱስ ከብዙ አመታት በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ያስተማራቸው ትምህርት ዛሬም ለእኛ ያስተምሩናል። ኢየሱስ ለአስራ አንዱ የተናገራቸው በማቴዎስ 28:18-20 ይገኛል፤ ይህ ቃል የእግዚአብሔርን ህዝብ በዘመናት ሁሉ ሲመራቸው ነበር።

**የቤት ስራ**: ማቴዎስ 28:16-20 አንብቡት።

**መልመጃ**:

1. ደቀ መዛሙርቱ የት ነው የሄዱት (ቁጥር 16)?

______________________________

2. እዚያ ለምን ሄዱ?

_______________________________________________

3. ባዩትም ጊዜ _________________________ ።

4. ___________________________________ግን ነበሩ።

5. ኢየሱስ ወደ እነርሱ መጣ። ምን ብሎ ተናገራቸው ቁጥር 18?

_______________________________________________

_______________________________________________

6. እንግዲህ_______________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________! (ቁጥር 19 -20)።

7. እርሱ ቃል የገባው ነገር ምንድነው (ቁጥር 20ለ)?

_______________________________________________

## ትምህርት

መፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔርን የምስራች አጠቃልለው የያዙ ሶስት የምልክት ቁጥሮች አሉ። ክፍሉን እያነበባችሁ ፃፏቸው።

1. ዮሐንስ 3:16-17

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

በዮሐንስ 3 ላይ እግዚአብሔር አለምን ሁሉ እንደወደደ ይናገራል። የእርሱ ፍላጎት ጥንትም አሁንም ሆነ ለወደፊት መላው ዓለም ከኃጢአት፤ ከሞት፤ እና ከዲያብሎስ ለማዳን ነው። እግዚአብሔር አብ ይህንን ፍቅሩን የገለፀው ለእርሱ ውድ የሆነውን ብቸኛውን ልጁን በመስጠት ነው። እርሱ ልጁን የሰጠበት ምክንያት በልጁ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው ነው። እግዚአብሔር አብ ልጁ ኢየሱስን የላከበት ዓላማ በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን ነገር ግን አለምን ለማዳን ነው!

2. ኤፌሶን 2:8-9

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

_______________________________________________

ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን የፃፋቸው እነዚህ ቃላት ዛሬም እኛ ማድመጥ ያለብን መልዕክት ነው፡፡ እኛ የዳነው በፀጋ ነው፤ እግዚአብሔር ለእኛ ለው ፍቅር በፍፁም በስራ የሚገኝ አይደለም ፤ እኛም ለዚህ የተገባን አይደለንም፡፡ እኛ የዳነው የእርሱ ስጦታ በሆነው በፀጋው ነው፡፡ የእርሱ ፍቅር ነፃ ስጦታ ነው፤ በምንም ዓይነት የግል ጥረት የሚገኝ አይደለም፡፡ ይህ ስጦታ የሚገኘው በእምነት ሲሆን ያም እምነት በኢየሱስ የመቤዠት ስራ ነው ፡፡ ለእኛ እግዚአብሔር የሚናገረን የእርሱ ልጅ ሁሉንም አድርጎታል፤ፈፅሞታል፡፡ *ተተለስታይ!*

3. ማቴዎስ 28:19-20

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በማቴዎስ 28 ኢየሱስ የሚነግረን ነገር ስለራሱ ስልጣን ነው፡፡ ይህ ስልጣን ለእርሱ የተሰጠው ከእግዚአብሔር አብ ነው፡፡ አሁን እርሱ ለደቀ መዛሙርት፤ ለእኛ እና ከእኛ በኂላ ለሚመጡ ሁሉ የሚናገረን፤ "ሂሱና ህዝቦችን ሁሉ ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው!" እያለ ነው፡፡ ይህ ግብዣ ለእኛ የቀረበ ነው፤ እርሱ በሰጠው ስም እንድናጠምቅ እና ለእርሱ ቃል ሰዎች እንዲታዘዙ እንድናስተምር ነው፡፡ ከሁሉም በላይ እስከ ዓለም ፍፃሜ ከእኛ ጋር እንደሚሆን ቃል ገብቶልናል፡፡ እነዚህ ቃላት የሚያስረዱን የእርሱ ልጆችና በመንግስቱ ውስጥ በመሆናችን እድለኞች መሆናችንን ነው፡፡ መታደላችን ደግሞ ሃላፊነት እንዳለበት ያሳየናል፤ ይህም ሃላፊነት የእርሱ መልዕክተኞች ሆነን የምስራቹን ቃል ለሰው ልጆች ሁሉ ማድረስ ነው ፡፡ እነዚህ ቃላት ሌሎችን የጌታን ቃል የማስተማር እና ራሳችንም የመማር ሃፊነት እንዳለብን ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ቃለት የሚሰጡን ተስፋ የእርሱን ከእኛ ጋር መሆንን ነው፤ እርሱ ከእኛ ጋር ሲሆን አዕምሮን የሚያልፍ ሰላምን ይሰጠናል፡፡

**ማስታወስ**

እነዚህ ሶስት ምንባቦች ሁልጊዜ የምናስታውሳቸው ናቸው፤ ምክንያቱም የእኛን ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ በእምነት የተገኘውን ያረጋግጥልናል፡፡ እኛ በህይወታችን ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በጋለ ስሜትና በተነቃቃ መንፈስ መሆን እንዳለበት እና ወደ ዓለም ሁሉ በመሄድ ሰዎችን ሁሉ የእርሱ ደቀ መዛሙርት እንድናደርግ የሚያሳስቡን እና የሚያዙን ናቸው፡፡

እነዚህን ጥቅሶች በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ ያልፃፋችሁ ከሆነ አሁን ፃፏቸውና በቃላችሁ ለማስታወስ መክሩ፤ ከማስታወስ ባለፈ ደግሞ ቃሉ ለጌታ ጥሪ እንድንታዘዝ የሚሞግተን ስለሆነ "ሂዱ፤ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው!" ለሚለው የኢየሱስ ቃል እንታዘዝ፡፡

**የትግበራ እቅድ**:

1. በህይወታችሁ ውስጥ እግዚአብሔር እናንተን ለወንጌል ተልዕኮ የጠራችሁን ያም "ሂዱ፤ ሰዎችን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው!" ብሎ አዝዞኛ ብላችሁ ያሰባችሁበትን ጊዜና ሁኔታ ለይታችሁ ፃፉ ______________________________

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

2. እግዚአብሔር እናንተን ወደ ዓለም ሁሉ እንደላካችሁ ማወቃችሁ በእናንተ ህይወት ላይ የእለት ተእለት ተግባራችሁን እና ሃላፊነታችሁን ስትወጡ ያመጣው ለውጥ ወይን ተፅዕኖ አለ?

   ______________________________________________________________________

   ______________________________________________________________________

**ፀሎት**

አዎን ጌታ ሆይ፤ ለአንተ እና አንተ ላቀረብከው የወንጌል ተልዕኮ ጥሪ የምሰጠው መልስ እሺ እታዘዛለሁ፤ እሄዳለሁ የሚል ነው። ጌታ ሆይ እኔ አንተ ለእኔ ያለህን ፍቅር፤ ለእኔ ኃጢአት እና በደል ይቅርታ የሚሰጠውን የአንተን ፀጋ የተረዳሁት በጣም በጥቂቱ ነው። በጣም ያስደነቀኝ ነገር ስለእኔ ሁሉንም ነገር የምታውቅ ቢሆንም እኔን ወዳጅህ ለማድረግ ጋበዝከኝ ። እኔ በጣም ማወቅ ያለብኝ ነገር አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር መሆንህን ነው። ሌላው የሚገርመኝ ነገር እና እምነቴን የሚረጋግጥልኝ ነገር አንተ ከእኔ ጋር መሆንህ ብቻ ሳይሆን አንተ በውስጤ መሆንህ ነው። ጌታ ሆይ ተጠቀምብኝ፤ በፊቴ ያስቀመጥከውን የአገልግሎት እድሎችን ማየት እንድችል ዓይኖቼን ክፈት። የአንተን ፍቅር በስራ ቦታ፤ በትምህርት ቤትለ በጎረቤቶቼ ዘንድ እና በቤቴ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ሁሉ እንዳካፍል እርዳኝ። ስለዚህ ትልቅ እድል፤ ኃላፊነት እና የቤት ስራ አመሰግንሃለሁ። በህይወት ዘመኔ ሁሉ በታማኝነት ላገልግልህ።

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

# ክለሳ

# የእግዚአብሔር ፍቅር፤ የእኛ ህይወት

*ክፍል አንድ እና ክፍል ሁለት*

## ክለሳ

እንኳን ደስ አላችሁ! *የእግዚአብሔር ፍቅር፣ የእኛ ህይወት* የሚለውን የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁለቱንም ክፍሎች አጠናቅቃችኋል። በዚህ ጥናት መሰረት ከአራቱ ወንጌላት፣ ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ እና ዮሐንስ ስለ የኢየሱስ መከራ፣ ስቅለት፣ሞት፣እና ትንሳኤ ታሪክ ተመልክተናል። በተጨማሪም ኢየሱስ ተላልፎ እንደሚሰጥ፣ ተከታዮቹ እንደሚክዱት፣ እንደሚገረፍ፣ እንደሚቀለድበት፣ እና እንደሚሰቀል አውቋል። በዚህ ሁሉ መከራ እና ስቃይ ውስጥ እርሱ ለአባቱ ፣እግዚአብሔር አብ ፈቃድ ታዛዥ ነበር። በአባቱ እንዲያከናውነው የተላከበትን ዓላማ እንደሚፈፅመው ያውቅ ነበር። በጥናታችን ውስጥ ከፋሲካ እራት በኋላ ከእራሱ ደቀ መዛሙርት ጋር ሆኖ ወደ ጌተሰማኒ የአትክልት ስፍራ ሄዶ በፀሎት ሲታገል እንደነበርም ተመልክተናል። የአስቆርቱ ይሁዳ ኢየሱስን ለወታደሮቹ ፣ሐናና ቀያፋ በመሳም አሳልፎ ሲሰጥም አይተናል። ኢየሱስ በጠላቶቹ ፊት በሚከሰስበት ጊዜ ወታደሮቹ ሲያላግጡበት፣ ሲያንገላቱት፣ ሲሰድቡት፣ ሲተፉበት እና በጥፊ ሲመቱት በፀጥታ ውስጥ ሆነን ተቀምጠን አይተነዋል። ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ጵላጦስ ተላከ፣ ጵላጦስም ምንም ነገር ስላላገኘበት ወደ ሔሮድስ ላከው። ሔሮድስም ኢየሱስ ተዓምራት ሲያደርግ ለማየት ቢጓጓም ኢየሱስ ግን ይህንን ባለማድረጉ በመከፋት ወደ ጵላጦስ መልሶ ላከው። ጵላጦስ "የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ የአይሁድ ንጉስ " የሚል ፅሁፍ ኢየሱስ በሚሰቀልበት መስቀል አናት ላይ እንዲሰቀል በማድረግ ኢየሱስ በስቅላት እንዲገደል ወሰነ፣ ኢየሱስም የተሰቀለው ማንነቱን እንደተጠበቀ ሆኖ ነው!

ኢየሱስ ዓለም ሁሉ እርሱ "*ተተለስታይ!*" ያለውን እንዲሰማ ይፈልጋል። ኢየሱስ እራሱን መስዋዕት አድርጎ ሲያቀርብ ከዚያ በፊት በብሉይ ኪዳን የነበረ አንድም መስዋዕት በብቃት ወደ ክርስቶስ መስዋዕትነት ያመላከተ የለም። እርሱ መስዋዕት ነው። እርሱ ስለኃጢአት የሚከፈል ዋጋ ነው። እግዚአብሔር የዓለም አዳኝ በሆነው ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የኃጢአት ይቅርታን እና ሰላምን ይሰጣል።

አሁን ጥናታችን የምንከልስበት ጊዜ ነው። ይህ ፈተና ሳይሆን እስአሁን ድረስ አስደሳች በሆነ መንገድ ያጠናናቸውን እንደገና የምንመለከትበትን እድል የሚሰጥ ነው። የኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ "እግዚአብሔር አብ እንደላከኝ እኔም እልካችኋለሁ" ብሎ የተናገረው ቃል ዛሬም እኛን ወደ እግዚአብሔር መንግስት አገልግሎት ያም እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ ዓለም ሁሉ እንዲድን በአለው እንቅስቃሴ እንድንቀላቀል ይጋብዘናል።

ተጨማሪ የክሮስ ኮኔክት ጥናቶች በነፃ ከድህረ ገፃችን ይገኛሉ።

የአገልግሎታችንን ድህረ ገፅ: www.crosscm.org.

አስተያየታችሁን መስማት እንፈልጋለን!

በዚህ አድራሻ እንገናኝs: admin@crosscm.org